በኢኮኖሚ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

(ECONOMIC CRIMES)

መስከረም-2006 ዓ/ም

<u>አዲስ አበባ</u>

ማውጫ *ገፅ*

መግቢያ I

. . . . II

ክፍል አንድ
በመንገሥት የኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች አጠቃላይ ፅንሰ ሐሳብና ፋይዳው

1.1 ትርጉም 1

1.2 በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በአገር ኢኮኖሚ የሚኖራቸው አንደምታ 2

1.2.1 በአገር ኢኮኖሚ ሉዓላዊነት ያለው አንድምታ 3

1.2.2 አገራዊ ኢኮኖሚ ከመገንባትና ነፃና ሕጋዊ የንግድ ውድድር ከማበረታት አንፃር 4

1.2.3 የህዝብ ጤናና ሞራል፣ ሰላምና ፀጥታ ከማስከበር አንፃር 5

ምዕራፍ ሁለት
በመንግሥት የኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ከኢፌደሪ የወንጀል ሕግ አንፃር

2.1 አጠቃላይ ድንጋጌዎች 8

2.2 ዝርዝር ድንጋጌዎች 12

2.2.1 በወርቅ በጥሬ ገንዘብ እና በውጭ አገር ገንዘብ በሕገወጥ መንገድ መነገድ 12

2.2.2 በከበሩ ማዕድናት ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ መነገድ 14

2.2.3 በመንግስት ገንዘብ አስተማማኝነት ላይ የሚደረግ የተንኮል ድርጊት . . . 14

2.2.4 ሕገወጥ በሆነ መንገድ የመንግሥትን ቀረጥ ወይም ግብር የመክፈል እንቢተኛነት 15

2.2.5 ግብር እንዳይከፈል ማነሳሳት 17

2.2.6 በመንግሥት የገቢ ምንጮች ላይ ጉዳት ማድረስ 20

2.2.7 ኬላ መስበር/ኮንትሮባንድ/ 23

2.2.8 በአገር ኢኮኖሚ በመንግስት ምኖፖል ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች 33
2.2.9 በአገር ኢኮኖሚ በመንግስት ምኖፖል ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች 34

ምዕራፍ ሶስት

በመንግስት ኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች በተግባር የሚያጋጥሙ ችግሮችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች

3.1 ችግሮች 36
3.1.1 የወንጀል ሕግና አዋጆች አጣጥሞ ከመተርጐም አንፃር ክፍተቶች የሚታዩ መሆናቸው፤.. 36
3.1.2 በኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ የተፈፀሙ ወንጀሎች ውስብስብ መሆንና የማስረጃ አሰባሰብ ሥርዓት ደካማ መሆን፣ 36
3.1.3 ደንቦችና መመሪያዎች ለሕዝቡ ተደራሽ አለመሆናቸው 36
3.1.4 የአስፈፃሚው ተቋማትና የዳኝነት አካል በኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ተጽኖ መቋቋም የሚያስችል አደረጃጀት መከተል 36
3.1.5 በኮንትሮባንድ ወንጀል የሚከሰሱ ሰዎች በዋስትና ከተለቀቁ በኃላ የመጥፋት አደጋ 37
3.2 *የመፍትሄ አቅጣጫዎች*_. 37
3.2.1 በኢኮኖሚና ገንዘብ ነክ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች የሚመለከቱ ሕጐች ተደራሽ ማድረግ 37
3.2.2 በኢኮኖሚ የገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ትርጉምና ይዘት ተቀራራቢ መለኪያ ማበጀት 37
3.2.3 በኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅም ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ለመከላከል የሚያስችል ስልት መዘርጋት 37
3.2.4 በኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ለመመርመር፣ ለመከራከርና ጥራት ያለው ውሣኔ ለመስጠት የሚያስችል አደረጃጀት ፣ ተቋማዊ ብቃትና ሙያዊ ክህሎት፣ እውቀትና አመለካከት ማሳደግ፣ . .37
3.2.5 የኢኮኖሚ ነክ ጉዳዩች የሚመለከቱ ችሎቶች ማደራጀት ፤ የተፋጠነ የፍትህ ሥርዓት መዘርጋት 37

3.2.6 የወንጀሉ ባሕርይ ዓለም አቀፍ ይዘት ያለው በመሆኑ ከሌሎች
አገሮችም ቅንጅታዊ አሰራር መፍጠር 38
❖ ዋና ዋና ዋቢ ፁሑፎች 39

መግቢያ

በመንግሥት ኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች መከላከልና በሂደት ማክሰም አገራዊ ፋይዳው ፈርጅ ብዙ ነው፡፡ በኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች መከላከል በሂደት ማክሰም ከአገር ሉዓላዊነት፣ ነፃና ሕጋዊ ንግድ ከማበረታታት ፣ የሕዝብ ጤና፣ ሠላምና ሞራል ከመጠበቅ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ዳኞችና ዓቃቤያነሕግ በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ሙያዊ ተግባራቸውን ሲያከናውኑ ከአዋጆቹ በስተጀርባ ያሉት የፖሊሲ ምክንያቶች ጠንቅቆ ማወቅ ተገቢ ነው፡፡ ኢኮኖሚ ነክ የወንጀል ዓይነቶች በወንጀል ሕጉና በልዩ አዋጆች ተመልክተዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል የገቢ ግብር አዋጅ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ፣ የጉሙሩክ አዋጅ፣ የብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ፣ የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃ አዋጅ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ዳኞችና ዓቃቢያነ ሕግም እነዚህን አዋጆችና የወንጀል ሕጉን አጣጥሞ በመተርጐም የሕግ አውጪው ሊያሳካ ያሰበው ዓላማና ግብ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች አተረጓጐም የወንጀል ሕግ ዓላማና ግብ የሕጋዊነት መርህ፣ የማስረጃ አመዛዘን ሥርዓት እና የውጤትና ምክንያት ትስስር ጠንቅቆ ማወቅ ይገባል፡፡ ይህ አጭር ማሰልጠኛ ጽሑፍ በሶስት ምዕራፎች የተከፋፈለ ነው፡፡ የመጀመሪያ ምዕራፍ በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች አጠቃላይ ጽንሰሐሳብ ይተነተናል፡፡ ሁለተኛው ምዕራፍ የወንጀል ሕጉ አጠቃላይ ድንጋጌዎችና ዝርዝር ድንጋጌዎች ይዳስሳል፡፡ ሶስተኛውና የመጨረሻው ምዕራፍ በተግባር የሚያጋጥሙ ችግሮችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች ያትታል፡፡ ሥልጠናው በተግባር የተደገፈ እንዲሆን በየደረጃው ባሉ የፌደራል ፍ/ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች ተመርጠው ለውይይት ይቀርባሉ፡፡ ሠልጣኞችም በንድፈ ሐሳብና በተግባር ያከበቱት ዕምቅ ዕውቀት በማካፈል ፍሬያማ የሥልጠና ጊዜ እንዲያደርጉት ይጠበቃል፡፡ በክፍል ውይይትና በቡድን ውይይት ጠቃሚ ትምህርት የሚገኝ በመሆኑ ዳኞችና ዓቃቢያነ ሕግ የወንጀል ሕጉና ልዩ አዋጆቹ በአግባቡ በመተርጐም ከሕጉ በስተጀርባ ያሉት የፖሊሲ ምክንያቶች ጠንቅቆ በማወቅና በመተግበር ተፈላጊው ፍትህ ማስመዝገብ ይቻላል፡፡

ሰልጣኞች ስልጠናውን ሲያጠናቅቁ

- በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ትርጉምና ባሕሪያት መሠረታዊ ዕውቀት ይጨብጣሉ፣

- በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች አጠቃላይ ጽንሰሐሳብ ይገነዘባሉ፣

|

- በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በአገር ኢኮኖሚ የሚኖራቸው አንድምታ ይረዳሉ፣
- በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በተመለከተ በወንጀል ሕጉና ልዩ ልዩ አዋጆች የተደነገጉት መሠረታዊ ጽንሰሐሳቦች በመረዳት በማጣጣም ለመተርጐም የሚያስችል መሠረታዊ ግንዛቤ ያገኛሉ፣
- በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች መካከልና በሂደት የማክሰም ሥራ ፖሊሲ ምክንያቶች ጠንቅቀው በማወቅ በዳኝነት ዓቃቤ ሕግነት ሙያቸው ሲሠሩ ተፈላጊው ፍትህ ይሰጣሉ፣
- የወንጀል ፍትሕ አስተዳደሩ በአገር ኢኮኖሚ ግንባታ የሚኖረው ሚና ይገነዘባሉ፣ የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ይነሳሳሉ፣
- በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ለመከላከል በተግባር የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች በመለየት የመፍትሄው አካል ይሆናሉ፣
- ኢኮኖሚነክ ወንጀሎች ቅንጅታዊ አሠራር የሚሹ በመሆናቸው የፍትህ ተቋማት ሙያዊ ነፃነታቸው በጠበቀ መልኩ ለጋራ ዓላማ በጋራ የመሥራት አስፈላጊነት ይገነዘባሉ፣
- በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የማፈጸሙ ወንጀሎች በተመለከተ በፌደራል ክልል ፍ/ቤቶች የሚሰጡ ውሳኔዎች በመምረጥ አስተማሪነታቸው ይገመግማሉ አስፈላጊውን ትምህርት ይወስዳሉ፤
- አስተማሪ ቅጣት በመወሰን ወንጀል ፈፃሚዎች እንዲታረሙ ማሕበረሰቡም እንዲጠነቀቅ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ተረድተው ለተግባራዊነቱ ይተጋሉ፣
- የወንጀል ሕጉና ልዩ ልዩ አዋጆች ከሕገመንግሥቱ የሰብአዊመብት መርሆዎች አንፃር በመቃኘት በአገር ደረጃ ወጥና ተገማች ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ግንዛቤ ያገኛሉ፣
- በአጠቃላይ ሰልጣኞች በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች አገራዊ አንድምታ፤ አገራችን የምትከተለው ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የልማት ጉዞ ነፃና ሕጋዊ የንግድ እንቅስቃሴ ከማበረታታት አንፃር፤ ኢኮኖሚው የሚፈልገው ገቢ ለመሰብሰብና ማሕበረሰቡ ተጠቃሚ የሚሆንበት ፍትህዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር፤ የሕዝቡ ጤና፣ ሞራል፣ ሠላምና ፀጥታ ለማስከበር ወንጀሉን መከላከል በሂደት የማክሰም አቅጣጫ

መከተሉ አማራጭ የሌለው መንገድ መሆኑ አውቀው ወሣኝ ሚና ሊጫወቱ እንደሚገባ ግንዛቤ ይወስዳሉ፣

መልካም ንባብ

||

ምዕራፍ አንድ

በመንግሥት የኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች አጠቃላይ ጽንሰ ሐሳብና ፋይዳው

1.1 ትርጉም

በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ዓይነትና ብዛት እንደ የአገሩ የሕግ አወጣጥ ሥርዓት የሚወሰን በመሆኑ ወጥ ትርጉም አለው ለማለት አይቻልም፡፡ ይሁንና በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ዓይነትና ብዛታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚያሠራ ትርጉም (working definition) ግን ሊሰጠው ይችላል፡፡ በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 346-353 በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ዓይነት ደንግጓል፡፡ የወንጀል ሕጉ በቀጣይ ክፍል እንደምንመለከተው የወንጀል ሕጉ እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች ልዩ ልዩ አዋጆች ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ ከእነዚህም መካከል የገቢ ግብር አዋጅ ፣ የጉምሩክ አዋጅ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ የብሄራዊ ባንክ አዋጅ የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃ አዋጅ መጥቀስ ይቻላል፡፡

በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ በተለይም በኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወጀሎች በዓይነት ከመጠቀሳቸው ውጭ ትርጉም አልተሰጠውም፡፡ የወንጀል ዓይነቶችና የሚያስከትሉት የወንጀል ተጠያቂነት ከመደንገጉ አንፃር የድንጋጌዎቹ ዝርዝር ፍሬ ነገር (ይዘት) ስናነበው ትርጉም ሰጪ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ለምሳሌ ኮንትሮባንድ ማለት ምን ማለት እንደሆነ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 352(1) እንዲሁም የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 ተመልክቷል፡፡

አለምአቀፍ ይዘት ያላቸው አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች የተለያየ ትርጓሜ የሚሰጣቸው መሆኑ ነው፡፡ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች በኢትዮጵያ ወንጀል ሕግ እንደወንጀል ድርጊት ከተደነገጉት ውጪ ሙስና፣ ማጭበርበር፣ አደገኛ ዕፅ ማዘዋወር ወዘተ የሚጨምር መሆኑን ያመለክታል፡፡ በኢኮኖሚ የገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎተ አለምአቀፋዊ ይዘቱ ሲታይ በርካታ መገለጫዎች አሉት፡፡ ከነዚህም መካከል፣

1. በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች በግለሰብ በአጠቃላይ ደግሞ በአገር ኢኮኖሚ (national economy) ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ መሆናቸውን፣

2. የወንጀል ድርጊቱ ውስብስብ ከመሆኑ አንፃር ልሒቃን (Intellectuals) የሚፈፅሙት ወንጀል መሆኑ፣

3. የወንጀል ድርጊቱ አፈጻጸም በአመጽ ላይ ያልተመሰረተ (non-violent crime) መሆኑ፣

4. በኢኮኖሚ እና በገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ድንበር ተሻጋሪ ሊሆኑ ይችላሉ፣

5. በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ከቴክኖሎጂ እድገት ጋር ከፍተኛ ትስስር ያላቸው መሆኑን፣

6. በማደግ ላይ ባሉ አገሮች በተለይም ጠንካራ የሆነ የሕግ ማስከበር ስርዓት በሌላቸው አገሮች የሚበዛ መሆኑ፣

በማጠቃለል በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ወጥ የሆነ ትርጉም ባይኖራቸውም (ማለትም ምን እንደሚያካትትና እንደማያካትት) የማጭበርበር ወንጀል፣ የአደገኛ ዕፅ ዝውውር፤ የሀሰት ገንዘብ ዝውውር፣ እምነት ማጉደል፣ ጉቦ፣ የተደራጀ ዘረፋ፣ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር፣ የታክስ ሲወራ፣ የውጭ ምንዛሪ በሕገወጥ መንገድ መስራት፣ የአዕምራዊ ንብረት ስርቆት፣ የባህር ላይ ውንብድና ወዘተ የሚያካትት ነው፡፡

1.2 <u>በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች በአገር ኢኮኖሚ የሚኖራቸው አንደምታ</u>

በኢኮኖሚና በገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች አገራዊ አንደምታቸው ከፍተኛ ነው፡፡ የተለያዩ አገሮች በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች አገራዊ ፋይዳቸው ከየአንዳንዱ አገር የፖሊሲ ምክንያት ሊወሰን ይችላል፡፡ በኢፌድሪ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 346-353 እና በሌሎች አዋጆች የተደነገጉት ኢኮኖሚ ነክ የወንጀል ድርጊቶች ከወንጀል ሕጉና አጠቃላይ የሕጉች የፖሊሲ ምክንያቶች ስንመረምር በሚከተሉት ነጥቦች ሊጠቃለል ይችላል፡፡

1.2.1 <u>በአገር ኢኮኖሚ ሉዓላዊነት ያለው አንደምታ</u>

አንድ ሉዓላዊ አገር መንግሥት፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የግዛት ሉአላዊነት አለው፡፡ መንግስት የተለያየ የልማት ስራዎች ለመስራት ገቢ ያስፈልገዋል፡፡ ግብር መጣልና መሰብሰብ የአንድ ሉአዓላዊ መንግስት የስልጣኑ መገለጫ ነው፡፡ የኢኮኖሚ ሉዓላዊነት

ለማረጋገጥ መንግስት ግብር የመሰብሰብ ስልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የወንጀል ሕጉ ወይም የተለያዩ አዋጆች ተጥሰው ከተገኙ ሕግ የማስከበር ስራ ለመስራት አጥፊዎች በሕግ ፊት ቀርበው እንዲቀጡ ያደርጋል፡፡ መንግስት በኢኮኖሚ እና በገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ለመከላከል ፈርጀ ብዙ ዲሲኘሊኖች የሚያጠቃልል አዋጆች ያወጣል፡፡ የወንጀል ሕጉ፣ አዋጆች ከሕገመንግስቱ በማስተሳሰር ከተመለከትነው እና ከተረጐምነው ከሕጐች በስተጀርባ ያሉ መሰረታዊ መርሆዎች እናገኛለን፡፡ በወንጀል ሕጉና ሌሎች አዋጆች መግቢያ (preamble) የተደነገጉት መሠረታዊ ነጥቦች በማፍታታት ከተመለከትናቸውና ከተረጐምናቸው በርካታ ሕገመንግስታዊ ጉዳዮች የሚዳሰሱ ሆነው ይገኛሉ፡፡ የወንጀል ሕጉ እንዲሁም የጉምሩክ፣ የገቢ ግብር፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጆች ስለግብር መጣልና መሰብሰብ በአጽንኦት ይገልጻሉ፡፡ እዚህ ላይ ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ፡፡ ይህውም መንግስት ለምንድነው ግብርና ታክስ የሚሰበስበው ? ግብርና ታክስ በመሰብሰብስ ምን ምን ተግባራት ያከናውናል ? የሚሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች በአግባቡ ካልተመለሱ የወንጀል ሕጉና፤ አዋጆቹ በአግባቡ ለመተርጐም ከማስቸገሩ በተጨማሪ የፖሊሲ ምክንያቱን ተረድተንም ሳንተረጉመው እንችላለን፡፡ ይህ ደግሞ የገቢ ሕጐች በአግባቡ ካልተተገበሩ መንግስት ያቀደውን ፈርጀ ብዙ የልማት ስራ በተፈላጊው መጠን እንዳይሳካ ሊያደርገው ይችላል፡፡

የኢፌድሪ ሕገመንግስት በመግቢያው ላይ ከደነገጋቸው መሠረታዊ የፖሊሲ አቅጣጫዎች አንዱ አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማሕበረሰብ መፍጠር እንደዋና ግብ ወስድዋል፡፡ ይህ እምቅ የሕገመንግስቱ ድንጋጌ አገላለፅ ከበስተጀርባው በርካታ ነገሮች ታሳቢ ያደርጋል፡፡ አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማሕበረሰብ ሊፈጠር የሚችለው በብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የተዋቀሩት ክልሎች የተመጣጠነ የእድገት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ መንግስት አገራዊ ገቢ ፍትሐዊ በሆነ መልኩ ለማዳረስ ገቢና የኢኮኖሚ ፖሊሲ ያስፈልገዋል፡፡ በሕገመንግስቱ ምዕራፍ 11 ከአንቀጽ 96-100 እንደተመለከተው የፌደራል መንግስትና ክልሎች ታክስና ግብር የመጣልና የመሰብሰብ ስልጣን እንዳላቸው በሕገመንግስቱ ተመልክተዋል፡፡ መንግስት ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ እድገት የማረጋገጥ፣ ማሕበራዊ አገልግሎቶች የማሟላት በተለይም አገራዊ ሀብት ፍትሀዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበት ስርዓት ወይም ሁኔታ የማመቻቸት(equitable distribution of wealth) ግዴታ እንዳለበት በሕገመንግስቱ አንቀጽ 41፣ 89(2) ተደንግጓል፡፡ መንግስት ከታክስና ግብር የሰበሰበው ገቢ ፍትሐዊ በሆነ አግባብ የማዳረስ ግዴታ ያለበት በመሆኑ

የታክስና ግብር ስርዓት ለዚህ አፈፃፀም እንደአንድ መሳሪያ ይጠቀምበታል ። በመሆኑም በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ በተለይም ከታክስና ግብር በተያያዘ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ከሕጉ መሠረታዊ መርሆዎች አንፃር ካልተመለከትነው ሕገመንግስቱ እንደግብ የደነገገው ተግባር ማሳካት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል።

በተለምዶአዊ አካሄድ የመንግስት ሚና ተብለው የሚታወቁ ተግባራት ቀረጥና ታክስ በመሰብሰብ ሰላምና ፀጥታ ማስከበር ፣ የመከላከያ ስርዓት መዘርጋት፣ ሕግ የማስከበር ስርዓት ነበር። አሁን ባለንበት የእድገት ደረጃ የመንግስት ሚና ግብርና ታክስ ከመሰብሰብ ባሻገር የሀይል አቅርቦት ሟሟላት፣ ግድቦች መስራት፣ የጤና ተቋማት ማስፋፋት የመኖሪያ ቤት ማሟላት፣ የማሕበራዊ ዋስትና አገልግሎቶች ማረጋገጥ እንደወሳኝ የመንግስት ሥራ የተወሰዱ ናቸው። ቀረጥና ታክስ በሌለበት ሁኔታ መንግስት ማህበራዊ ፍትሕ (አገልግሎት) ማሟላት ይቅርና ሕልውናውን ሊከስም ይችላል። በመሆኑም በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጥባቸው ይገባል። አስፈፃሚውና የዳኝነት አካሉ የሕጉ የፖሊሲ ምክንያቶች በሚገባ ጠንቅቆ ማወቅና መተግበር ይጠበቅባቸዋል። የኢፌድሪ የወንጀል ሕግና ሌሎች አዋጆች ከግብርና ታክስ ባሻገር ከዱር እንስሳት፣ በወርቅና ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮች የሚፈፀሙ ወንጀሎች ተመሳሳይ አላማና ግብ ያላቸው መሆኑን መረዳት ይቻላል።

1.2.2 *<u>አገራዊ ኢኮኖሚ ከመገንባት፣ ነፃና ሕጋዊ የንግድ ውድድር ከማበረታታት አንፃር</u>*

ነፃና ሕጋዊ የንግድ ውድድር አገራዊ ኢኮኖሚ ከመገንባት አንፃር ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ግብርና ታክስ የማይከፍል ከሆነ የታክስ ሲወራ፣ የኮንትሮባንድ ንግድ በተስፋፋበት አገር ነፃና ሕጋዊ የንግድ ውድድር ሊኖር አይችልም። የወንጀል ሕግ መግቢያ በግልፅ እንደደነገገው " የወንጀል ሕጉ የአገሪቱን የኢኮኖሚ እድገት ለማፋጠን የሚያስችልና የተረጋጋ የነፃ ገበያ ስርዓት እንዲጐለብት የሚያደርግ ----" መሆኑ የሚያሳይ ነው። በመሆኑም የግብርና ታክስ ሕጐችነፃነና ሕጋዊ የንግድ ውድድር ከማስፈን አንፃር ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ።

ነፃና ሕጋዊ የንግድ ሥርዓት ካለ አገራዊ ኢኮኖሚ (wealth creation) የመገንባት ጉዳይ የተሳለጠ ያደርገዋል። የግብርና ታክስ ዓላማ እና መሠረታዊ ባህሪያት ስንመለከታቸው ገቢ ማሳደግ፣ የኢኮኖሚ መረጋጋት መፍጠር፣ የዋጋ ግሽበትና እጥረት መቆጣጠር፣ የኢኮኖሚ አለመመጣጠን መቀነስ ወይም ማመጣጠን፣ ቁጠባ ማበረታታት፣ የሥራ ዕድል መፍጠር፣ የውጭ ንግድ ማበረታታት፣ መሠረታዊ

የፍላጐት ፍጆታዎች ተደራሽ ማድረግ ወዘተ ነው፡፡ የታክስ ሲወራና ኮንትሮባንድ በተስፋፋበት ማሕበረሰብ ከፍሲሉ የተጠቀሱ መሠረታዊ ዓላማዎች ማሳካት አይቻልም፡፡ በአንዳንድ ባለሙያዎች አስተያየት ፖለቲካዊ ሉዓለዊነት ያለ ኢኮኖሚያዊ ዓቅምና ነፃነት ትርጉም እንደሌለው ይከራከራሉ፡፡ መንግሥት የተለያዩ ማሕበራዊ ተቋማት በመመሥረት የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ ሥርዓት ይፈጠራል፡፡ በመሆኑም ነፃና ሕጋዊ የንግድ ውድድር ባለበት ሀገራዊ ኢኮኖሚ ይገነባል፡፡ ሀገራዊ ኢኮኖሚያ ከተገነባ ደግሞ ኢኮኖሚያዊና ኢኮኖሚያዊ ያልሆኑ ጥቅሞች ያስገኛል፡፡ ኢኮኖሚያዊ ጥቅምች የመንግሥት ገቢ መጨመር፣ የሥራ ዕድል መፍጠር፣ ኑሮ ማሻሻል እንደ ውጤት የሚወሰዱ ሲሆኑ ኢኮኖሚያዊ ያልሆኑ ጥቅሞች ደግሞ ሰላምና መረጋጋት ፣ ዴሞክራሲና የሕግ የበላይነት ለማስፈን ያግዛል፡፡ በመሆኑም በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅመች የሚፈጸሙ ወንጀሎች በመከላከልና በመቆጣጠር ነፃና ሕጋዊ የንግድ ውድድር እንዲሰፍን መሥራት ይጠይቃል፡፡

1.2.3 <u>የህዝብ ጤናና ሞራል፤ ሰላምና ፀጥታ ከማስከበር አንፃር</u>

መንግሥት የኮንትሮባንድ ንግድ የሚቆጣጠርበት ዋና ዓላማ ገቢ መሰብሰብ ብቻ ሳይሆን የንግድ ሥርዓቱ በዓለም ተወዳዳሪ ማድረግ፣ ብሄራዊ ደሕንነት መጠበቅ፤ የዜጐች ጤንነት ወዘተ መሠረት ያደረገ መሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 622/2001 መግቢያ መረዳት ይቻላል፡፡ መንግሥት በአገሪቱ ክልከላ ወይም ገደብ የተደረገባቸው ዕቃዎች በመቆጣጠር የማሕበረሰቡን ጤና፣ ሞራልና ሰላም መጠበቅ ነው፡፡ ከተለያዩ አገሮች ተመኩሮ እንደምንመለከተው በተደራጀ መልኩ የሚፈጸሙ የአደገኛ ዕጽ ዝውውር የሰላም ጠንቅ መሆኑ እንገነዘባለን፡፡ በታጠቁ ቡድኖች የሚደረግ የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴ በመንግሥት ገቢ፣ ነፃና ሕጋዊ ንግድ ላይ ከሚደርሰው ተጽዕኖ አንፃር የስጋት ምንጭ ነው፡፡ በመሆኑም መንግሥት የጉምሩክ ሕግ ከደነገገበት ምክንያት አንዱ የኮንትሮባንድ አደጋ የመከላከል ጉዳይ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በምትከተለው ፖሊሲ አንዳንድ ዕቃዎች ገደብ የተደረገላቸው ሲሆን ሌሎች ደግሞ ወደ አገር እንደሚገቡ የሚመለከተው አካል ፈቃድ የሚጠይቁ ናቸው፡፡ አንዳንድ ለሕክምና አገልግሎት የሚውሉ መድሀኒቶች በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ወይም በመድሀኒት ቁጥጥር ፈንድ ባለሥልጣን ፈቃጅነትሲገቡ ይችላሉ፡፡ አንዳንድ ነገሮች ደግሞ በፍጽሞ የተከለከሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለምሣሌ ከማሕበረሰቡ ሞራል የማይራመዱ የልቅ ወሲብ ፊልሞች ፤ የአደንዛዥ ዕጽ ዝውውር ክልከላ ከተደረገባቸው ነገሮች አንዱ

ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከሚትከተለው ሥርዓት አንፃርም የጦር መሣሪያ በአደባባይ መሸጥና መግዛት የተከለከለ ነው፡፡ በሌላ በኩል አገራዊ ፋይዳ ያላቸው የኢትዮጰያ ብቸኛ ንብረት የሆኑ ዕጽዋት ብርቅየ የዱር እንስሳት ከኢትጵያ እንዲወጡ አይፈቀድም፡፡

ኮንትሮባንድ የመቆጣጠር ጉዳይ የሕልውና ጉዳይም የሚሆንበት ሥርዓት ይኖራል፡፡ ደረጃቸው በሚገባ ያልተፈተሹ የኮንስትራክሽን ማተሪያሎች፣ መድሀኒቶች፤ የምግብ ፍጆታዎች ቁጥጥርና ክትትል ሳይደረግባቸው ለሕ/ሰቡ ከተሠራጩ አደጋው የከፋ ይሆናል፡፡ ደረጃው ያልጠበቀ ወይም የመጠቀምያ ጊዜ ያለፈበት መድሃኒት መውሰድ ሕይወት ሊያሳጣ ይችላል፡፡ በመሆኑም መንግሥት በኮንትሮባንድ የሚገቡ ዕቃዎች በተመለከተ ጠበቅ ያለ ዕርምጃ ካልወሰደ የማሕበረሰቡ ጤና፣ ሞራልና ሰላም ማስከበር አይችልም፡፡

በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች አገራዊ ፋይዳቸው በሚገባ ካልተጤነ የሚያስከትሉት ጉዳት ከፍተኛ ነው፡፡ በኢፌዲሪ የወንጀል ሕግና ሌሎች አዋጆች ለዚህ ርዕስ የተሰጠው ትርጉም የተወሰኑ ጉዳዮች ብቻ የሚመለከት ቢመስልም ከድንጋጌዎቹ አጠቃላይ ይዘት ስንመለከተው የኢኮኖሚ ወንጀሎች ሰፊ ይዘት ያላቸው ከአፈጻጸማቸው አንፃርም የተለየ ስልትና ባሕርይ የሚያመለክቱ ናቸው ፡፡ በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በመንግሥት የኢኮኖሚ አውታሮች፤ በነፃና ሕጋዊ የገበያ ሥርዓት ስጋት የሚፈጥሩ፤ ኢኮኖሚያዊ ሠላም የሚያናጉ ናቸው፡፡ የሥነ ሕግ ተማራማሪዎች የኢኮኖሚ ወንጀሎች አድማስ በመወሰን የተቸገሩ ቢሆንም በሀብታሞች የሚፈጸም ወንጀል፣(ለምሳሌ ማታለል፣ የግብርና ታክስ ሲወራ)፣ ከድርጊቱ አፈጻጸም በሰላማዊ መንገድ የሚፈጸም እንጂ እንደ ስርቆትና ውንብድና ማሕበረሰብ የሚንጫጫቡቸው ችግሮች አይደለም፡፡ የአፈጻጸም ስልቱ በግለሰብ ደረጃ፣ በቡድን ወይም ድንበር ዘለል ልሆን ይችላል፡፡ በኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ለመከላከል የተለያዩ አዋጆች ወጥቷል፡፡ ይሁንና የወንጀል መከላከል ሥራውን አልፈው የተፈፀሙ ወንጀሎች መኖራቸው ግልጽነው፡፡ በተለይም ታዳጊ አገር ከመሆናችን አንፃር ነፃና ሕጋዊ የንግድ ውድድር የሚያዳክሙ ድርጊቶች እየታዩ ነው፡፡ እኩል የውድድር ሥርዓት ከሌለና የተዛባ ከሆነ መንግሥት ተገቢው ግብርና ታክስ መሰብሰብ አይችልም፡፡ አንዱ ንግድ ፈቃድ በማውጣት ሲሠራ ሌላደግሞ በዘፈቀደ የሚነግድበት፤ የምንዛሪ ሥርዓት የሚያዛቡ ሕገወጥ ግብይቶች ከተሰፋፋ፣ ጥራታቸው ጥያቄ ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች

ወደ ተጠቃሚዎች ከቀረቡ የውድድር ሥርዓቱ ፣ የሕዝብ ጤናና ሞራል በከፍተኛ ደረጃ አደጋ ውስጥ ይገባል፡፡

<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. ዓቃቤያን ሕግና ዳኞች በመንግሥት ኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ሲመለከቱ አገራዊ ፋይዳው ምን ያህል ትኩረት ሰጥተው ይወስናሉ?
2. በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ከሕዝቡ ጤና፣ ሞራልና ፀጥታ አንፃር ያላቸው ትስስር ምን ይመስላል ?

ምዕራፍ ሁለት

በመግሥት የኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ከኢፌድሪ የወንጀል ሕግ አንፃር

2.1 አጠቃላይ ድንጋጌዎች

የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ መግቢያ እንዳመለከተው ተበታትነው የሚገኙ ድንጋጌዎች የማጠቃለል ሥራ መሠራቱን ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል ዜጐች በአንድ ጉዳይ በተለያየ የሕግ አንቀጽ እየተከሰሱ የሚቀጡ ከሆነ የዜጐች የእኩልነት መርህ የሚፃረር መሆኑ ከወንጀል ሕግ መግቢያ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ አጠቃላይ መርህ ሲሆን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 3 በግልጽ እንደደነገገው የወንጀል ሕጉ እንደተጠበቀ ሆኖ ቅጣት የሚደነግጉ ደንቦችና ልዩ ሕጐች የተጠበቁ መሆናቸው ያሳያል፡፡ ይሁንና በልዩ ሁኔታ ካልተወሰነ በቀር የቅጣት አወሳሰን መርሁ ግን ከወንጀል ሕጉ የተጣጣመ እንዲሆን ግድ ይላል፡፡ በተግባር እንደምንመለከተው ዓቃቤያነሕግ በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ በተፈፀሙ ወንጀሎች ክስ ሲያቀርቡ ከወንጀል ሕጉ ይልቅ አዋጆች አዘውትረው ሲጠቅሱ ይሰተዋላል፡፡ ለምሣሌ ኮንትሮባንድ ፣ የውጭ ምንዛሪ መሥራት፣ ግብር አለመክፈል፣ የዱር እንስሳት ወይም የዱር እንስሳት ውጤቶችን ያለፈቃድ ይዞመገኘት በተመለከተ የሚቀርቡ ክሶች የብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ 591/2000፣ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ 541/1999፣ የገቢ ግብር አዋጅ 286/1994፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 ዓ.ም ሲጠቅሱ ይስተዋላል፡፡ ለዚህ ዋና ምክንያት ተብሎ የሚወሰደው በአዋጆች የተደነገጉ የቅጣት መጠን ከወንጀል ሕጉ ከፍያለ በመሆኑ ነው፡፡

ዓቃቢያነ ሕግ እና ዳኞች በአዋጆች ብቻ ላይ ተመስርተው ውሳኔ የሚሰጡ ከሆነ የወንጀል ሕጉ መቼ ነው ተፈፃሚ የሚሆነው የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ የወንጀል ሕጉ ኮንትሮባንድ በተመለከተ የወንጀል ተጠያቂነት የደነገገ ሲሆን የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 በተመሳሳይ ደንግጓል፡፡ እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ የወንጀል ሕጉ ከመውጣቱ በፊት በልዩ አዋጅ የተደነገጉ የኢኮኖሚ ገንዘብ ጥቅሞች ለመከላከል የወጡ አዋጆች ከወንጀል ሕጉ የበለጠ የሚያስቀጡ ከሆነ የተሻለው ሕግ ለተከሳሽ ጥቅም ሲባል መውሰድ የሚለው የሕገመንግሥቱ አንቀጽ 22(2) እና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 6 አፈጻጸም ጥያቄ ውስጥ ሊገባ ይችላል፡፡

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 343፣ 344 እና 354 አጠቃላይ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 343 ልዩ ሕጐች በመጣስ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በተመለከተ መሠረታዊ መርሆዎች ደንግጓል፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 343 ሶስት መሠረታዊ ፍሬነገሮች አካቷል፡፡ የመጀመሪያው መሠረታዊነጥብ ልዩ ሕጐች (የኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች) ሥልጣን ባለው የመንግሥት አካል የወጡ መሆን አለባቸው፡፡ በሕገመንግሥቱ እንደተደነገገው ሕግ የማውጣት ሥልጣን የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ሲሆን አስፈፃሚው የሕዝብ ተወካዮችም/ቤት በሚሰጠው ውክልና መሠረት ደንብ የማውጣት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ (ሕገመንግሥት አንቀጽ 77(13) ይመለከተዋል)፡፡ የወንጀል ሕግ የማውጣት ሥልጣን ለሕዝብ ተወካዮችም/ቤት የተሰጠ ነው፡፡ ክልሎች የወንጀል ሕግ ማውጣት የሚችሉት በፌደራል መንግሥት የወንጀል ሕግ በግልጽ ባልተመለከቱ ወይም ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ብቻ መሆኑ በሕገመንግሥት አንቀጽ 55(5) በግልጽ ተመልክቷል፡፡ እዚህ ላይ የሚነሳው መሠረታዊ ጥያቄ የወንጀል ሕግ የማውጣት ሥልጣን ለምን ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ተሰጠ የሚልነው፡፡ ቡዙ ምክንያቶች ማስቀመጥ የሚቻል ቢሆንም በዋናነት ሊጠቀስ የሚችለው የወንጀል ጉዳዮች በዜጐች፤ ህይወት፣ ነፃነት ንብረት የሚጣል ቅጣትና ገደብ በመሆኑ የሰብአዊ መብት ጥሰት ለመከላከል የሕዝብ ውክልና በተሰጠው ሕግ አውጪ እንዲወጣ መደረጉ ተገቢነው፡፡

በሕግ ባለሙያዎች መካከል የሚያከራክር አንድ መሠርታዊ ጉዳይ አለ፡፡ ይህውም የሕዝብ ተወካዮችም/ቤት አስፈፃሚው ደንብና መመሪያ እንዲያወጣና ደንብና መመሪያ መተላለፍ የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል መሆኑ ቢደነገግ ከሕግ አወጣጥ መርህ አኳያ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚል ክርክር ይነሳል፡፡ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91/1/ እንዲሁም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 26(1) ከፍ ሲል በተጠቀሰው አግባብ ደንብና መመሪያ መተላለፍ የወንጀል ተጠያቂነት እንደሚያስከትል የደነገጉ ሆነው ይገኛሉ፡፡ የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎትም በመዝገብ ቁጥር 43781 በአማርኛ ቋንቋ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ያልወጣ በእንግልዝኛ የተፃፈ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ መመሪያ በተመለከተ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በመዝገብ ቁጥር 43781 የተደረገው ክርክር እና የፍ/ቤቱ ድምዳሜ ከአጠቃላይ የሕግ አወጣጥ ሥርዓት እንዴት ይመለከቱታል?

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 343 በግልጽ እንደደነገገው የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትለው ድርጊት በሕግ መሠረት ሥልጣን ባለው የመንግሥት አካል መውጣት እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ከዚህ በተያያዘ የሚነሳው ጥያቄ የወንጀል ሕግና ተጠያቂነት እንዴት ይደነገጋል የሚል ነው፡፡ የወንጀል ሕግ እንዴት ይደነገጋል የሚለውን ጠቃሚ ነጥብ ከማየታችን በፊት ስለሕግ አንዳንድ ነገሮች እንናንሳ፡፡ ሕግ የሕግ የበላይነት ለማረጋገጥ አንዱ መሣሪያ በመሆኑ መንግሥት በሚያወጣው ሕግራሱ ተጠያቂ መሆኑ፤ ሥልጣን ባለው አካል የሚወጡ ሕጐች የተወሰነ የሕ/ሰብ ክፍል ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት የማይደነገጉ፤ የሕጋዊነት መርህ የሚከተሉ፤ የሥርዓታዊ ሂደት ሙብት (due process of law) የሚጠብቁ፤ ለማሕበረሰቡ አስቀድመው በቂማስጠንቀቅያ የሚሰጡ በተለይም ሕጐች ለሕዝብ ግልጽ ማድረግ ለትረጉም ያልተጋለጡና አሻሚያልሆኑ፤ የተፈፃሚነት ወሰናቸውም ከወጡበት ወደኃላ ሳይሆን ወደ ፊት እንዲሆን ማድረጉ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው መርህ ነው፡፡ ለአጠቃላይ ግንዘቤ ከፍሲል የተጠቀሰው ወስደን መጀመሪያ ወደ ተነሳው ጥያቄ ስንመለስ የወንጀል ሕግ መደንገግ ማለት ምን ማለት ነው የሚለውን ነጥብ ሕገ መንግሥቱ ዝርዝር ማብራሪያ የሚሰጥ ባይሆንም ከአጠቃላይ የሕግ አወጣጥ ሥርዓት አንፃር ስንመለከተው የሚከተሉት ነጥቦች ያካትታል፡፡ የመጀመሪያው ነጥብ የወንጀል ድርጊት ነው የተባለው ከመስም ይጀምራል፡፡ ይህ ማለት ኮንትሮባንድ፣ ስርቆት፣ ውንብድና፣ ግድያ ወዘተ በማለት ይዘረዘራሉ፡፡ ሁለተኛው ነጥብ የወንጀሉ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ይዘረዝራል፡፡ ለምሣሌ ስርቆት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 665 ማቋቋሚያ ፍሬነገሮች አካቷል፡፡ ሶስተኛ የወንጀል ድርጊቱ መተላለፍ የሚያስከትለው የቅጣት መነሻና መድረሻ ይደነግጋል፡፡

የወንጀል ሕግ ተጠያቂነት ስያሜው፣ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሩ በዝርዝር ካልተቀመጠ ለአፈጻጸም አስቸጋሪ እንደሚሆን ባለሙያዎች ይከራከራሉ፡፡ በአዋጅ ቁጥር 622/2001፣ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ አዋጅ ቁጥር 591/2001 አንቀጽ 91 እና 26 (1) በቅደም ተከተል የተቀመጡ ድንጋጌዎች ለአፈጻጸም ያስቸግራሉ የሚል ነው፡፡ መጀመሪያ የሚነሳው ክርክር ደንብ መተላለፍ መደበኛ የወንጀል ተጠያቂነት አያስከትልም የሚልነው ፡፡ ደንብና መመሪያዎች አዋጅ የማስፈጻም ዓላማ ያላቸው በመሆኑ የወንጀል ተጠያቂነት የሚደነግግ ድርጊት የሚያቋቁም ፍሬ ነገር መያዝ አይችሉም የሚል ነው ፡፡ ከአፈጻጸም አንፃርም የሚነሳ ክርክር አለ፡፡ የጉምሩክ አዋጅ

ቁጥር 622/2001 ከወጣ በኋላ በ2004 የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ወደኋላ ተመልሰው እንዴት ተጠያቂነት ያስከትላሉ የሚል ነው፡፡ በሌላ በኩል በደንብ መተላለፍ የሚያስጠይቁና በመደበኛ ወንጀል የሚያስጠይቁ ድርጊቶች ተለይተው ካልተቀመጡ ፍትሀዊነት ይጋፋል የሚል ክርክርም ይነሳል፡፡ ሕግ አውጪው ደንቦችና መመሪያዎች የአዋጅ ክብደት እንዲኖራቸው ከፈለገ በአዋጅ መልክ ለምን አይወጡም የሚል የክርክር ሐሳብም ይነሳል፡፡ እነዚህና ተመሳሳይ ሁኔታዎች የወንጀል ተጠያቂነት በደንብና መመሪያ ከማስቀመጥ አንፃር በጥንቃቄ ልታዩ ይገባል፡፡

ሁለተኛው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 343 የተቀመጠው መሠረታዉ ነጥብ በሕግ መሠረት ሥልጣን ባለው አካል የወጡ ሕጐች በነጋሪት ጋዜጣ ሊደነገጉ ይገባል የሚል ነው ፡፡ የወንጀል ሕጉ ልዩ ሕጐች በመጣስ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ወይም በክልል መንግሥታት የሕግ ጋዜጣ መውጣት ያለበት መሆኑ ተመልክቷል፡፡ በፌደራል ደረጃ ያለው ልምድ በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው የሚወጡት አዋጆችና ደንቦች ናቸው፡፡ አካራካሪ የሚሆነው የመመሪያ ጉዳይ ነው፡፡ መመሪያ የሕግ ክብደት ኖሮት የወንጀል ተጠያቂነት ለማስከተል በነጋሪት ጋዜጣ ሊታተም ይገባል፡፡ በሰበር መዝገብ ቁጥር 43781 የተነሳው አንዱ መሠሪታዊ ጭብጥ ብሄራዊ ባንክ በእንግሊዘኛ ያወጣው መመሪያ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ አልወጣም የሚል ነበር፡፡ መመሪያ መጣስ በኮንትሮባንድ የሚያስጠይቅ ከሆነ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ካልወጣ ለሕዝቡ እንዴት ተደራሽ ሊሆን ይችላል? የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትሉ ድርጊቶች በነጋሪት ጋዜጣ ማውጣት የወንጀል ሕግ አንቀጽ አንድ ግብ ለማሳካት ወሳኝ ነው፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀጽ አንድ “ስለ ወንጀሎችና ቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቅያ መስጠት” የሚለውን ግብ ያሳካል፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2(2)፣ 23(1) ሕገመንግሥት አንቀጽ 22(1) ስለ ሕጋዊነት መርህ በተመሳሳይ ደንግጓል፡፡ ሶስተኛው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 343 መሠረታዊ ነጥብ ቅጣቱ በልዩ ወንጀል ሕግ የሚጣል ቢሆንም የቅጣት አወሳሰን ሥርዓቱ የወንጀል ሕግ መርሆዎች ተፈፃሚ ስለመሆናቸው ነው፡፡ ይህ ማለት ስለቅጣት ማክበድና ማቅለል፣ ስለግብረአበርነት፣ ስለቅጣት መገደብ ወዘተ ወንጀል ሕጉ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

በወንጀል ሕግ አንቀጽ 343(2) የገንዘብ መጠኑ እስከ አሥር ሺ የሚደርስ ከሆነ በደንብ መተላለፍ ብቻ የሚያስጠይቅ መሆኑ ነው፡፡ የዚህ ወንጀል ሕግ ድንጋጌ የብሄራዊ ባንክ ወይም የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከሚያወጡዋቸው የወንጀል

ተጠያቂነት የሚያስከትሉ ድንጋጌዎች የገንዘብ መጠን ሊቃረን ይችላል። ለምሣሌ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በወጣው መመሪያ ከ200,00 የኢትዮጵያ ብር በላይ ይዞ ከአገር መውጣት በአዋጅ ቁጥር 622/2001 ተጠያቂነት እያስከተለ እንዲነበር ግልጽ ነው። ይህ ደግሞ በዚህ ርዕስ መግቢያ እንደተጠቀሰው ለተከሳሹ የተሻለው ሕግ ተፈፃሚ ከማድረግ አንፃር ሊያከራክር ይችላል።

አጠቃላይ ድንጋጌዎች ከሆኑት አንድ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 344 ነው። የዚህ ሕግ አንቀጽ ዋና ዓላማ የወንጀል ቅጣት አይነትና መጠን መወሰን ነው። ልዩ የወንጀል ድንጋጌዎች የወንጀል ተጠያቂነት ብቻ ያስቀመጡ ከሆነ ወይም ወደ ወንጀል ሕጉ በግልጽ የማይመሩ ከሆነ ፍ/ቤቱ የወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ድንጋግዎችና መደበኛ የቅጣት አወሳሰን ሥርዓት ሊከተል እንደሚገባ እስራት ወይም መቀጮ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 90፣92፣106 እና 107 ተፈፃሚ ሊሆን ይገባል። በሌላ በኩል የወንጀል ድርጊቱ ከባድ ከሆነ የቅጣቱ መጠን ከፍ የሚል መሆኑ፣ ከቅጣቱ በተጨማሪ ሌሎች ተጨማሪ ዕርምጃዎች ማዘዝ ይቻላል። የገቢ አዋጅ ቁጥር 286/1994 እና የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁ የጥፋተኞች ስም ዝርዝር በጋዜጣ መውጣት እንዳለበት ተመልክቷል።

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 354 ወንጀል የሚያከብዱ ሁኔታዎች ደንግጓል። በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅም የተፈጸሙ ወንጀሎች የከሣሹ የዘወትር የሞያ ሥራ ከሆነ ወንጀሉ የተሠራበት ሀብት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ የመቀጮና የእስራት ቅጣቱ ከፍ ይላል። የወንጀል ሕግ አንቀጽ 345 በተመሳሳይ አስተዳደራዊ ዕርምጃዎች ሊወሰዱ እንደሚችሉ የወንጀል ተጠያቂነት ከአስተዳደራዊ ቅጣት ነፃ የማያደርግ መሆኑ ተመልክቷል።

2.2 ዝርዝር ድንጋጌዎች

2.2.1 በወርቅ በጥሬ ገንዘብ እና በውጭ አገር ገንዘብ በሕገወጥ መንገድ መነገድ

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 346 በወርቅ፣ በጥሬ ገንዘብ እና በውጭ አገር ገንዘብ በሕገወጥ መንገድ መነገድ በተመለከተ ዝርዝር ነገሮች ደንግጓል። በኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ወርቅ፣ ገንዘብ በተለይም ከምንዛሪ ጋር በተያያዘ በብሄራዊ ባንክ የቁጥጥር ሥርዓት ሥር የሚካሄድ ነው። በዚህ የሕግ አንቀጽ ሰዎች የሚጠየቁት ሁለት መሠታዊ ነገሮች ሲረጋገጡ ነው። አንደኛው ሥራውን ፍቃድ የሚያስፈልገው ከሆነ ያለፍቃድ መሥራቱ ሲረጋገጥ ሲሆን ሁለተኛው ነጥብ ፍቃድ ቢኖርም በሕግ የተጣሉ ገደቦች በመተላለፍ ድርጊቱ የተፈጸመ ከሆነ የወንጀል ተጠያቂነት ያስከትላል። ወንጀሉ

ከሚያቋቁሙ ነገሮች መግዛት፣ ከውጭ አገር ማስገባት፣ መላክ በአደራ ማስቀመጥ፣ መመንዘር፣ የተሸጠ ለሽያጭ የቀረበ ወንጀል የተፈጸመበት ሀብት የመውረስ ደንብ መጽናቱ የተጠበቀ ሆኖ ከአሥር አመት በማይበልጥ እስራት እና እስከ ብር ሃምሣ ሺ ብር መቀጮ ያስቀጣል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 591/2000 የወንጀል ሕግ የደነገጋቸው ተመሳሳይ ፍሬ ሐሳቦች አካቷል፡፡ የውጭ ምንዛሪ ከማስተዳደር አንፃር በአንቀጽ 20/1/ እንደተመለከተው" ማንኛውም ሰው ከባንኮች ወይም ፍቃድ ከተሰጣቸው መንዛሪዎች ጋር ካልሆነ ወይም ከብሔራዊ ባንክ የተለየ ፍቃድ ካላገኘ በቀር በውጭ ምንዛሪ ግብይት ለመሠማራት አይፈቀድለትም" በማለት ደንግጓል፡፡ የወንጀል ተጠያቂነት በተመለከተ በአዋጅ አንቀጽ 26/1/2/3/ በተመለከተው አግባብ እንደሚጠየቅ፣ ቅጣቱን በተመለከተ የወንጀል ሕጉ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር እስከ 15 አመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን መቀጮ ደግሞ እስከ 100ሺ ብር ይደርሳል፡፡ ከወንጀል ሕጉ አንፃር ከተመለከትነው በብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2000 የተደነገገው መቀጮና እስራት ከፍተኛ መሆኑ ነው፡፡ መንግስት ወርቅና፣ የውጭ ምንዛሪ በተመለከተ የተለየ ትኩረት የሰጠበት ምክንያት ለአገር ኢኮኖሚ ካላቸው ፋይዳ መሆኑ መገመት ይቻላል፡፡

በወርቅ፣ በጥሬ ገንዘብ እና በውጭ አገር ገንዘብ በሕገወጥ መንገድ መነገድ ወንጀል መሆኑ በወንጀል ሕጉና በብሄራዊ ባንክ አዋጅ ቁጥር 591/2002 እና 592/2002 የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል መሆኑ ግልጽ ቢሆንም በአፈጻጸም ረገድ ግን ችግሮች ይከሰታሉ፡፡ በዓ/ሕግ በሚቀርቡ ክሶች ክሱን ለማስረዳት ሲቸገር ይታያል፡፡ የፌዴራል ዓ/ሕግ በትዕግስት ስዩም ይህደጉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመሰረተው ክስና ፍ/ቤቱ በኮ/መ/ቁ 90851 በሰጠው ፍርድ ዓ/ሕግ እንደ ክሱ አላስረዳም የሚል ነው፡፡ ዓ/ሕግ በክሱ ግልጽ እንዳደረገው ተከሳሿ የባንክ ሥራ ለመስራት የሚያስችል የብሄራዊ ባንክ ፈቃድ ሳይኖራት በህገ ወጥ መንገድ የሐዋላ ሥራ በመስራት የውጭ አገር የተለያዩ ገንዘቦችን/የአሜሪካን ዶላር፣ዩሮ/ ቢሮ በመክፈት በአዲስ አበባ አራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 10 ዱባይ ኮስሞቲክስ መደብር ውስጥ ለተለያዩ ግለሰቦች ሕገ ወጥ የሐዋላ አገልግሎት በመስጠት በኢንተርኔት በኮምፒውተር በመታገዝ እ.ኤ.አ ከ16/08/2010 እስከ 30/06/2010 ድረስ ድምሩ 64,346.21 የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ሀገሪቱ እንድታጣና ጉዳት እንዲደርስባት በማድረጓ በፈጸመችው የባንክ

ሥራ አዋጅ መጣስ ወንጀል ተከሳለች የሚል ነው፡፡ ተከሳሿ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለቷ ዓ/ሕግ ማስረጃ አቅርቦ አሰምቷል፡፡ የዓ/ሕግ ምስክሮች በተከሳሿ ቤት ምንዛሪ መደረጉ ሳይክዱ እሷ ግን አልነበረችም በማለታቸው በነጻ ተለቃለች፡፡ በክርክር ሂደቱ ግልጽ የሆነው ነገር ምንዛሪ በተከሳሽ ቤት መካሄዱ ነው፡፡ ተከሳሿ በቦታው አልነበርኩም በማለቷ ብቻ ከክሱ ነጻ መሆኗ ተገቢ ነውን? የውጭ አገር ምንዛሪ በተከሳሽ የንግድ ድርጅት መደረጉ ሰዎች ገንዘብ የመጣላቸው መሆኑ እየተነገራቸው መውሰዳቸው ተረጋግጧል፡፡ እዚህ ላይ በጥንቃቄ መታየት ያለበት የምርመራ ክፍሉና ዓ/ሕግ በምንዛሪ የሚከሰሱ ሰዎች የማስረጃ አሰባሰብ ሥርዓቱ በጥንቃቄ መሆን ይገባል፡፡ ድርጊቱ ወንጀል ሆኖ መታወጅ ብቻውን በቂ ስለማይሆን የምርመራ ክህሎትና ብቃት በማሳደግ አገሪቷ የውጭ ምንዛሪ እንዳታጣ ከፍተኛ ሥራ መሰራት አለበት፡፡

2.2.2 በከበሩ ማዕድናት ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ መነገድ

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 347 የወንጀል ሕግ አንቀጽ 346 ተከታይ ነው፡፡ የወንጀል አፈጻጸም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 346 በተደነገገው አኳኋን ከሆነ ቅጣቱም በተመሳሳይ በዚህ የወንጀል ሕግ አንቀጽ ይካተታል፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 347 የከበሩ ማዕድናት በማለት የተወሰኑ ነገሮች የዘረዘረ ሲሆን ሌሎችም እነዚህን የመሳሰሉ በማለት ታልፏል፡፡ ወርቅ፣ፕላቲኒየም፣ዩራኒየም በምሳሌነት ተቀምጠዋል፡፡ በከበሩ ማዕድናት በዋናነት የመወሰን ስልጣን ያላቸው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ እና የማዕድን ሚኒስቴር ናቸው፡፡ እነዚህ ተቋማት የከበሩ ማዕድናት ለአገር ኢኮኖሚ በተለይም የውጭ ምንዛሪ ከማግኘት አንጻር ያላቸው ጠቀሜታ መሰረት በማድረግ እንደሚሰሩ ይጠበቃል፡፡ የወንጀል ሕጉና ሌሎች ልዩ ሕጎች የወንጀል ተጠያቂነት ማስከተሉ በከበሩ ማዕድናት ላይ ሊፈጸም የሚችለው ወንጀል ለመከላከል ያግዛል፡፡

2.2.3 በመንግስት ገንዘብ አስተማማኝነት ላይ የሚደረግ የተንኮል ድርጊት

በወንጀል ሕግ አንቀጽ 348 የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትሉ ድርጊቶች ሁለት ናቸው፡፡ አንደኛው የአገሪቱ የገንዘብ ምንዛሬ እንዲረክስ ለማድረግ ከባንክ ወይም ወደ ባንክ ለማስገባት በሕግ ግዴታ ከተጣለባቸው ሌሎች ድርጅቶች ገንዘብ እንዲወጣ ያደረገ ወይም ያነሳሳ ወይም የዋስትና ሰነዶች ወይም የግዴታ ሰነዶች በጅምላ በመሸጥ ዋጋቸው ዝቅ ማድረግ ነው፡፡ የገንዘብ ምንዛሪ በተማከለ ሥርዓት የሚመራ ነው፡፡ ማንኛውም ሰው ጉዳት ለማድረስ እንደሚችል እያወቀ ድርጊቱ መፈጸሙ ሲረጋገጥ ነው

የሚቀጣው፡፡ በኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ባንኮችና የኢንሹራንስ ተቋማት አክስዮን በመሸጥ ካገኙት ጠቅላላ የአክሲዮን ሽያጭ ለባለ አክስዮኖች ጥቅም ሲባል በብሄራዊ ባንክ እንዲያስቀምጡ ይገደዳሉ፡፡ በሌላ በኩል ወንጀል ፈጻሚው ግለሰብ ምንዛሪ የማርከስ ዓላማ ይዞ መስራቱ ሲረጋገጥ ብቻ ነው የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትለው፡፡ በኃላፊነት የሚጠየቁት የወንጀል ድርጊቱ ዋና ፈጻሚዎች ብቻ ሳይሆኑ የማነሳሳት ድርጊት የሰሩ ሰዎችም ጭምር ነው፡፡ የግዴታ ሰነዶች በጅምላ በመሸጥ ዋጋው ዝቅ ማድረግም የወንጀል ተጠያቂነት ያስከትላል፡፡ የግዴታ ሰነዶች (Share or Bonds) የታወቀ የመሸጫ ዋጋ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ በኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት የአክሲዮን ሽያጭ ከፍና ዝቅ ለማድረግ የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ መኖሩ ግልጽ ባይሆንም በመንግስት የገንዘብ አስተማማኝነት ላይ የሚፈጸም የወንጀል ድርጊት ከተፈጸመ ተጠያቂነት ያስከትላል፡፡

ሁለተኛው ነጥብ የዋስትና ወይም የግዴታ ሰነዶች ዋጋቸው ዝቅ ማድረግ ተጠያቂነት ማስከተሉ እንደተጠበቀ ሆኖ የዋስትና ሰነዶች ወይም የግዴታ ሰነዶች ሌላ ሰው እንዳያወጣ ማድረግ፣ ወይም የዋስትና ወይም የግዴታ ሰነዶች እንዳይገዙ ማሰናከል የወንጀል ተጠያቂነት ያስከትላል፡፡ የዋስትና ሰነዶች (Bonds) ወይም የግዴታ ሰነዶች (Securities) በአንድ አገር የንግድ እንቅስቃሴና በአጠቃላይ የሀገር ኢኮኖሚ የመገንባት ጉዳይ በማፋጠን በኩል ጥሩ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በመሆኑም የአክሲዮን ዋጋ ማውጣትና ለሽያጭ ማቅረብ የሚያሰናክል ድርጊት መፈጸም የወንጀል ተጠያቂነት ያስከትላል፡፡

2.2.4 <u>ሕገወጥ በሆነ መንገድ የመንግሥትን ቀረጥ ወይም ግብር የመክፈል እንቢተኛነት</u>

የግብር እና ታክስ አስፈላጊነት በዚህ ጽሑፍ መግቢያ በአጭሩ ተዳስሰዋል፡፡ በተለይም በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ከአጠቃላይ አገራዊ ገቢ ከፍተኛ ቦታ ሊይዝ ይችላል፡፡በአገራችን የግብር መሰብሰብ ሥርዓቱ ደካማ መሆኑ፣ የታክስ መሠረቱ መጥበብ፣ የግበር ከፋዬች የፈቃደኝነት ማነስ፣ የግብር ባለሥልጣኑ የማስፈጸም ብቃት ማነስ ተደምሮ መንግሥት ተገቢ የሆነው ግብር መሰብሰብ እየቻለ አይደለም፡፡ ግብር በተመለከተ የወንጀል ሕጉ፣ የገቢ ግብር አዋጅ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ግብር አለመክፈል በወንጀል ተጠያቂነት ያስከትላል በማለት ደንግጓል፡፡

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 349 ግብር የመክፈል እንቢተኛነት የወንጀል ተጠያቂነት ለማስከተል አንደኛ የግብር መክፈል ግዴታው በሕግ አግባብ ሊወሰን ይገባል፡፡ ሁለተኛ

ግብር የተጣለው የመወሰን ሥልጣን ባለው አካል መሆን አለበት፡፡ በኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ግብር የመጣልና የመሰብሰብ በዋናነት ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የተሰጠ ነው፡፡ ይሁንና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ብቸኛው ግብር ሰብሳቢ ተቋም ግን አይደለም፡፡ ክልሎች፣ የአዲስ አበባና ድሬደዋ መስተዳደሮች በሕግ አግባብ ግብር የመወሰንና የመሰብሰብ ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያ ግልጽ መሆን ያለበት ግብር በሕግ የተደነገገ ሥልጣን ባለው አካል የተወሰነ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 349/1/ የተወሰኑ ጉዳዮች ዘርዝረዋል፡፡ ለምሣሌ ከመሬት፣ ከንብረት ወይም ከልዩ ልዩ ገቢ በአይነትም ሆነ በገንዘብ የሚከፈል ግብር ማናቸውም ቀረጥ ወይም ታክስ እንዲከፍል በሕግ አግባብ ሲጠየቅ እንቢተኛ ከሆነ የወንጀል ኃላፊነት ያስከትላል፡፡

በዚህ ሕግ አንቀጽ ሥር ግልጽ መሆን ያለባቸው ነጥቦች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ነጥብ በኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት በምን በምን ጉዳዩች ላይ ግብር በአይነት ሊጠየቅ ይችላል የሚል ነው፡፡ በተለያየ ጊዜ የወጡ የግብር ማስከፈያ አዋጆች ገቢ ሰብሳቢው ተቋም በጥሬ ገንዘብ የሚቀበል መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም እንደ ጥያቄ ሊነሳ የሚችለው መንግሥት መቼ ነው ግብር በአይነት የሚጠይቀው የሚል ነው፡፡ ሁለተኛው ነጥብ አንድ ሰው እንቢተኛ ነው የሚባለው በሕግ አግባብ ተጠይቆ በአግባቡ የማይክፈል መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ እንቢተኛ ነው የምንለው በሕግ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት አለመክፈሉን ሲረጋገጥ ነው ወይስ በጊዜ ገደብ ውስጥ ባይከፍልም ግልጽ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው በኃላ እንቢተኛ ሆኖ ከተገኘ ነው የሚለው ያከራክራል፡፡ በሌላ በኩል ግብር መክፈል ከመክፈል አቅም ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የመክፈል አቅም የለኝም የሚል ክርክር በማንሳቱ እንቢተኛ ሊባል ይገባል ወይ? በማለት የሚጠይቁ የሕግ ባለሙያዎች አሉ፡፡

በወንጀል ሕግ አንቀጽ 349/2/ እንደተመለከተው እንቢተኛነቱ ዛቻን፣ የኃይል ሥራን፣ የእጅ እልፊትን ወይም በጦር መሣሪያ የመገልገል መሣሪያ አንስቶ የመቃጣትን ወይም ሁከትን ወይም አመጽን አስከትሎ ከሆነ አግባብነት ያላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡ ግብር ከፋዩ መክፈል ያለበትን ነገር አለመክፈሉ ሳይበቃ የግብር አስገቢው ተቋም ሠራተኞች ላይ ጉዳት ማድረሱ ከተረጋገጠ በተደራራቢ የወንጀል ድርጊት ይጠየቃል፡፡

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 349 ላይ የተመለከቱት የወንጀል ተጠያቂነት ድርጊቶች በገቢ ግብር አዋጅ 286/1994 አንቀጽ 96 እንዲሁም የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 49 ግብር ያልከፈለ እንደሆነ ወንጀል እንደተፈፀመ ይቆጠራል በማለት ደንግጓል፡፡ በእነዚህ ሁለት አዋጆች ግብር አለመክፈል ብቻ ሳይሆን አለማስታወቅም እንደ ወንጀል ድርጊት ተደንግጓል፡፡

በዚህ ጽሑፍ መግቢያ እንደተመለከተው የወንጀል ሕጉ፣የተለያዩ የገቢ ግብር አዋጆች እንዴት ተጣጥመው ይተረጐማሉ የሚለውን ጥያቄ ማንሳታችን ይታወሳል፡፡ በወንጀል ሕጉና በልዩ የገቢ የግብር አዋጆች የተቀመጡት የቅጣት መጠን ልዩነት ይታያል፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 349/1/ የተላለፈው ከአንድ አመት በማይበልጥ ቀላል እስራትና መቀጮ የሚያስቀጣ ሲሆን በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 96 እና በተጨማሪ እሴት ታክስ እዋጅ አንቀጽ 49 እንደተመለከተው ከአምስት አመት የማያንስ እስራት ያስቀጣል፡፡ በወንጀል ሕጉና በልዩ የገቢ ግብር አዋጆች የተደነገገው ቅጣት ልዩነት ካለው የትኛው ሕግ ተፈፃሚ ይሆናል የሚል ጥያቄ ያነሳል፡፡ የወንጀል ሕጉ በአንቀጽ 3 ሥር ልዩ የወንጀል ሕጐች የተጠበቁ መሆናቸው ደንግጓል፡፡ ይሁንና የገቢ ግብር አዋጅ 286/1994፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 ከወንጀል ሕጉ በፊት የወጡ ከመሆናቸው አንፃር የወንጀል ሕግ አንቀጽ 6 እና የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 22/1/ እና /2/ የተሻለው ሕግ ለተከሣሽ በሚመች መንገድ ተፈፃሚ ማድረግ የሚል ጽንሰ ሐሳብ እንዴት ይታያል የሚል መሠረታዊ የሕግ አተረጓጐም ጥያቄ ያስነሳል፡፡

<u>የመወያያ ጥያቄ</u>

የወንጀል ሕጉ፣ ልዩ ልዩ ኢኮኖሚክነክ አዋጆች እንዲሁም ሕገመንግሥቱ በተጣጣመ መልኩ እንዴት መተርጐም ይቻላል ? እርሱዎ እንደዳኛ፤ ዓቃቤ ሕግ በተግባር እንዴት ያስተናግዱት ነበር? ለምን?

<u>2.2.5 ግብር እንዳይከፈል ማነሳሳት</u>

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 350 ግብር እንዳይከፈል ማነሳሳት የወንጀል ተጠያቂነት ያስከትላል በማለት ደንግጓል፡፡ የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 101 እና የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ አንቀጽ 45 ተመሳሳይ ድንጋጌዎች ያካተቱ ሲሆኑ ከተጠያቂነት ደረጃ አንፃር ግን የተለየ ትርጉም ያለው ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ግብር ከፋዩ ግለሰብ ወይም ድርጅት ግብር ለመክፈል ፈቃደኛ ቢሆንም ሶስተኛ ወገኖች ግብር ከፋዩን በማነሳሳት

እንዳይከፍል ሊያደርጉት ይችላሉ። ማነሳሳት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 36 የተመለከተ ሲሆን ማነሳሳት ማለት አስቦ ሌላ ሰው በመጐትጐት ተስፋ በመስጠት፣ በገንዘብ በስጦታ በማስፈራራት ወይም በማናቸውም ዘዴ አንድ ወንጀል እንዲደረግ ያግባባ እንደሆነ ነው። አነሳሹ የሚቀጣው የወንጀል ድርጊቱ የተሞከረ እንደሆነ ነው። ምክንያቶች ከተገኙም ቅጣት ማቅለል እንደሚቻል፣ ዋና ወንጀል አድራጊው ያደረገው ወንጀል አነሳሹ ከፈለገው በላይ ከሆነ ተጠያቂ እንደማይሆን ተመልክቷል። አነሳሹ በመርህ ደረጃ የሚቀጣው ለታሰበው ወንጀል ሕጉ በደነገገው ቅጣት ልክ ነው። ይሁንና ከወንጀል ድርጊቱ አፈፃፀም አነሳሹ የቅጣት ማቅለያ ተጠቃሚ ሲሆን ዋና ወንጀል አድራጊው ግን ተጠቃሚ ላይሆን ይችላል።

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 350/1/ ማንም ሰው በአድራጐት፣ በስጦታ፣ በንግግር፣ በዛቻ ወይም በማናቸውም ሌላ ዘዴ ሌላ ሰው በሕግ የተደነገገው ቀረጥ ወይም ግብር እንዳይከፈል ያነሳሳ እንደሆነ በወንጀል ይጠየቃል።

የማነሳሻ መንገዶች ቡዙ መሆናቸው ከሕጉ መረዳት ይቻላል። ይሁንና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 350/1/ የወንጀል ድርጊቱ አፈፃፀም አስቦ ወይም በቸልተኝነት ስለመሆኑ አልተመለከተም። የወንጀል ሕግ አንቀጽ 36 ማነሳሳት የተረጐመበት አግባብ ለዚህ ሕግ አንቀጽ ተፈፃሚ ካልተደረገ በስተቀር የወንጀል ሕግ አንቀጽ 350/1/ ሥር የሐሳብ ክፍሉን አልተመለከተም። በመሆኑም ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት የተፈጸመ መሆኑና አለመሆኑ ካልተለየ በአፈፃፀም ረገድ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። በሌላ በኩል የወንጀል ድርጊቱ አፈፃፀም ከባድ ከሆነ ለምሣሌ የወንጀል ድርጊቱ የተስፋፋ ከሆነ ወይም አመጽ መቀስቀስ ወይም ባለሥልጣንን ለማስወገድ ማነሳሳትን ወይም ተመሳሳይ ድርጊቶች የወንጀል ተጠያቂነት ተደራራቢ ያደርገዋል።

ግብር እንዳይከፈል ማነሳሳት የወንጀል ተጠያቂነት ማስከተሉ ግልጽ ነው። ይሁንና የተጠያቂነት ደረጃው ምን ሊሆን ይችላል የሚለው ነጥብ ያከራክራል። የወንጀል ሕግ አንቀጽ 36 ዋና ወንጀል አድራጊና አነሳሽ መኖራቸው ያመለክታል። የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 55 እንዲሁም የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 101 ስለአነሳሽነት የተለየ ትርጓሜ ይዘዋል። የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅና የገቢ ግብር አዋጅ መርዳት ወይም ማበረታታት የተረጐመበት አግባብ ተመሳሳይ ነው። "በማናቸውም ሰው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንዲጣሱ የረዳ፣ ያበረታታ፣ ያነሳሳ ወይም በምስጢር የተባበረ እንደሆነ እንደዋንኛው

ጥፋተኛ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በመጣስ ጥፋት ይፈፅማል"፡፡ በማለት የወንጀሉ ማቋቋሚያ ፍሬነገር አስቀምጠዋል፡፡

ሁለቱም አዋጆች አነሳሽ እንደ ዋና ጥፋተኛ ተጠያቂ ይደረጋል የሚል ድንጋጌ አካቷል፡፡ ይህ ማለት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 36 ከተመለከቱት መርሆዎች የተለየ አቀራረጽ የሚያሳይ መሆኑ ነው፡፡ ግብር እንዳይከፈል ያነሳሳ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ካሉ አነሳሺ መሆኑ ብቻ ተጠቃሚ የሚያደርገው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 36 ተፈፃሚ አይሆንም ማለት ነው? በወንጀል ሕግ አንቀጽ 36 አነሳሺ ዋና ወንጀል አድራጊው የማያገኘው የቅጣት ማቅለያ ጥቅም ያገኛል ማለት ነው፡፡ የገቢ ግብር አዋጅና የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ በተመሳሳይ ወንጀል ተጠያቂ የሆነው አነሳሺ የቅጣት ማቅለያ ተጠቃሚ መሆኑ አከራካሪ ያደርገዋል፡፡ ዋና ወንጀል ፈፃሚና አነሳሺ እንደየተሳትፎአቸውና ግላዊ ሁኔታቸው መሠረት በማድረግ ቅጣት ይወሰንባቸዋል፡፡ ከፍሲል እንደተጠቀሰው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 36፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ 285/1994 አንቀጽ 55 እንዲሁም የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 101 በመተላለፍ ተጠያቂ የሚሆኑ ወንጀል ፈፃሚዎች በቅጣት አወሳሰን ረገድ እንዴት ሊስተናገዱ ይገባል የሚል መሠርታዊ ጥያቄ ማንሳቱ ተገቢ ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ መነሻ የሆነው በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ እና የገቢ ግብር አዋጅ አነሳሺ እንደዋነኛው ጥፋተኛ ተጠያቂ ይሆናል የሚል አነጋገር ነው፡፡ ልዩ አዋጆች ዝርዝር የቅጣት አወሳሰን መርሆዎች ያላካተቱ ከሆነ የወንጀል ሕጉ ተፈፃሚ እንደሚሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 3 ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም ዓቃቢያነሕግና ዳኞች ስለአነሳሺ የተጠያቂነት ደረጃ እና ቅጣት ሲወሰኑ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 36(3) ሁለተኛው ዓርፍተነገር ጽንሰሐሳብ በአጽንኦት ሊመለከቱት ይገባል፡፡

በወንጀል ሕግ አንቀጽ 350/2/ የደነገጋቸው የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ አንቀጽ 51 እና የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 98 ተደንግጓል፡፡ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሥራ ማሰናከል የወንጀል ተጠያቂነት ማስከተሉ የግብር አስገቢው ተቋም ሥራውን በአግባቡ ለማካሄድ ያስችለዋል፡፡

<u>*የመወያያ ጥያቄ*</u>

የአዋጅ ቁጥር 285 1994፣ 286/1994 አንቀጽ 101 እና 55 ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 350፣ 32 እና 36 እንዴት ይታያል? ያነሳሳ ግለሰብ እንደ ዋነኛ ጥፋተኛ ተወስዶ መቀጣቱ ተገቢ ነው ይላሉ? ለምን?

2.2.6 በመንግስት የገቢ ምንጮች ላይ ጉዳት ማድረስ

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 351/1/ በዋናነት ያተኮረው የግብር አወሳሰን ሥርዓቱ የሚያዛቡ ድርጊቶች መከላከል ላይ ነው፡፡ የወንጀል ድርጊቱ በማንኛውም ሰው ሊፈጸም የሚችል ሆኖ በአፈጻጸም ረገድ ግን ታስቦ የሚፈጸም ድርጊት መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ለመንግስት ግምጃ ቤት ገቢ ሊሆን የሚገባውን ማናቸውም ዓይነት ግብር ቀረጥ ወይም ሌላ ክፍያ በከፊል ወይም በሙሉ እንዳይከፈል ማድረግ የወንጀል ኃላፊነት ያስከትላል፡፡ ወንጀል ፈጻሚው ድርጊቱን የፈጸመው ለራሱ፣ ለሌላ ግለሰብ ወይም ድርጅት ጥቅም መሆኑ በተጠያቂነት ደረጃው የሚያመጣው ለውጥ የሌለ መሆኑ ከወንጀል ህጉ መረዳት ይቻላል፡፡ የወንጀል ህግ አንቀጽ 351/1//ሀ/ እና /ለ/ ሥር የወንጀሉን ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ተዘርዝረዋል፡፡ የመጀመሪያው መስፈርት ቀረጥ ወይም ግብር ሊወሰንበት የሚገባውን ዕቃ ወይም ካፒታል ለሚመለከተው ባለሥልጣን እያወቀ ሐሰተኛ መረጃ መስጠት ነው፡፡ ሁለተኛው መስፈርት የወንጀል ድርጊቱ አፈፃፀም በማናቸውም ዘዴ ሊፈጸም የሚችል ሆኖ የመንግሥት አካላት ከስህተት እንዲወድቁ፣ እያወቀ እውነቱን ወደ ሐሰት መለወጥ ወይም ነገሩን በስውር ወይም ሐሰተኛ ገቢ ወይም የፈጠራ ሂሣብ በማዘጋጀት ድርጊቱ የተፈጸመ ከሆነ ነው፡፡

የግብር ባለሥልጣኑ ቀረጥና ግብር ለመጣል እውነተኛ መረጃ ይፈልጋል፡፡ ትክክለኛ መረጃ መቅረቡ ለግብር ከፋዩና ለግብር አስከፋዩ ባለሥልጣን ጠቀሜታው የላቀ ነው፡፡ ሐሰተኛ መረጃ ከቀረበ የግብር ባለሥልጣኑ መሰብሰብ የሚገባውን ገቢ ሊያገኝ አይችልም፡፡ ግለሰቦች መክፈል የሚገባቸው ቀረጥና ታክስ ካልከፈሉ ደግሞ ነፃና ሕጋዊ የንግድ ውድድር ይጐዳል፡፡ መንግሥትም ገቢ ሰብስቦ ፈርጀ ብዙ የልማት ሥራዎች ማከናወን አይችልም፡፡ የወንጀል ድርጊቱ አፈፃፀም ግን አስቦ፣ እያወቀ መፈጸም እንዳለበት የወንጀል ሕጉ ደንግጓል፡፡ ይህ ማለት በቸልተኝነት በሚፈጸሙ ድርጊቶች ሐሰተኛ መረጃ ያቀረበ ወይም የፈጠራ ሂሣብ ያዘጋጀ አይጠየቅም እንደማለት ነው፡፡ የወንጀል ሕግ በዚህ ነጥብ ዙሪያ ከተጨማሪ እሴት ታክስ፣ የገቢ ግብር አዋጅ መሠረታዊ ልዩነት ይታይበታል፡፡ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ አንቀጽ 50 ተመሳሳይ ፍሬ ሐሳብ አካቷል፡፡ ይሁንና የወንጀል ድርጊት አፈፃፀሙ ታስቦ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ሊሆን እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ አንቀጽ 50/3/ እና የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 97/3/ "የሐሰት መግለጫ የሰጠው ወይም መካተት የሚገባው ነጥብ እንዲካተት ያልተደረገው ሆን ተብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት የሆነ

እንደሆነ" በማለት ደንግጓል፡፡ ይህ ማለት የወንጀል ሕጉ ላይ ያልተካተተው የከባድ ቸልተኝነት ተጠያቂነት መኖሩ በሁለቱም አዋጆች ተካቷል፡፡ ከዚህ በተመሳሳይ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 93/1/ /ሀ/ ሥር ለጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም በቀረበ ዴክላራሲዩን ላይ ያልተመዘገበ ወይም ሐሰተኛ መግለጫ የተሰጠበት እቃ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ወይም አነስተኛ ቀረጥና ታክስ ተከፍሎበት ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ ያደረገ" የወንጀል ኃላፊነት ይኖራል በማለት ደንግጓል፡፡ ቸልተኝነት በተመለከተ ግን በዚህ የሕግ አንቀጽ አልተካተተም፡፡

የቅጣት አወሳሰን ሥርዓት በተመለከተ የወንጀል ሕጉ ከአሥር አመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራትና ከአንድ መቶ ሺ ብር በማይበልጥ መቀጮ እንደሚያስቀጣ ሲደነግግ፣ የጉምሩክ አዋጅ አንቀጽ 93/1/ /ሀ/ የተመለከተውን መተላለፍ ከ7-10 አመት ጽኑ እስራትና የዕቃው መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ በእቃው ላይ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር በሚመጣጠን የገንዘብ መቀጮ እንደሚያስቀጣ ከሕጉ መረዳት ይቻላል፡፡ የተጨማሪ እሴት ታክስና የገቢ ግብር አዋጆች የሐሰት ወይም አሳሳች መረጃ በማቅረብ ለሚፈጸም የወንጀል ድርጊት እንደሁኔታው በተለይም ሊከፈል ይገባ ከነበረው የግብር መጠን የተለያየ ቅጣት ደንግጓል፡፡ ለምሣሌ በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 97/3/ /ሀ/ ላይ እንደተመለከተው" የመግለጫው ትክክለኛ ያለመሆን ሊደረስበት ያለመቻሉ ሊከፈል የሚገባው ግብር ከብር አንድ ሺ በማይበልጥ አንሶ እንዲከፈል የሚያደርግ ከሆነ ግብር ከፋዩ ከብር ሃምሣ ሺ በማያንስ እና ከብር አንድ መቶ ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እና ከአምስት አመት በማያንስ እና ከአሥር አመት በማይበልጥ እሥራት" ያስቀጣል በማለት ደንግጓል፡፡ ከዚህ መረዳት እንደምንችለው በወንጀል ሕግ፣ በገቢ ግብር አዋጅ፣ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ እና በጉምሩክ አዋጅ ለተመሳሳይ አይነት ድርጊትና አፈፃፀም የተለያየ የቅጣት መጠን መደንገጉ ነው፡፡

በወንጀል ሕግ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ የገቢ ግብር አዋጅ እና የጉምሩክ አዋጅ የሚታየው አንድ መሠረታዊ ልዩነት የወንጀል ድርጊቱ በግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሠራተኞች የተፈጸመ ከሆነ የሚጠየቁበት ሥርዓት ነው፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 351/2/ ወንጀል ፈፃሚው ባለሥልጣን ወይም ሠራተኛ ከሆነ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 407 በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል ተጠያቂ እንደሚሆን ተመልክቷል፡፡ የጉምሩክ አዋጅ አንቀጽ 89፣90 ባለሥልጣናትና ሠራተኞች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 407/1/ /2/ መሠረት የሚጠየቁ መሆናቸው ይገልጻል፡፡

የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ እና የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 53 እና አንቀጽ 99 በአዋጆች ላይ በተቀመጡ የቅጣት አይነቶች እንደሚቀጡ ነው፡፡ እነዚህ አዋጆች የወንጀል ሕግ ከመውጣቱ በፊት የተደነገጉ በመሆናቸው ወደ ወንጀል ሕግ እንዲመሩን የማይጠበቅ ቢሆንም በቅጣት አወሳሰን ረገድ የሚታየው ክፍተት በተለይም የተሻለው ሕግ ከመውሰድ አንፃር የሚነሳው ክርክር ግን ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም፡፡ የገቢ ግብር አዋጅ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ተመሳሳይ አይነት ቅጣት ደንግጓል፡፡ በግብር ባለሥልጣኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ጥፋተኛነታቸው በሕግ አግባብ ሲረጋገጥ ከ10 አመት በማያንስ ከ20 አመት በማይበልጥ እስራት እና ከ50 ሺ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣሉ፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 407/2/ ሥር ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘው እስራቱ ከ7 እስከ 15 አመት እንደሚቀጣ፣ መቀጮ ደግሞ ከ50 ሺ ብር እንደማይበልጥ ተደንግጓል፡፡ በእስራት ቅጣት መነሻና መድረሻ የሚታየው ልዩነት በፍትሕ ሥርዓቱ ወይም በተከሣሾች መብት ላይ የራሱ የሆነ ተጽዕኖ እንደሚኖረው መገመት አያዳግትም፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቶችን በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች የጥፋተኝነትና ቅጣት አወሳሰን ረገድ ሕጐቻችን እንዴት አጣጥመን መተርጐም እንዳለብን በአጽንኦት ልንመለከተው የሚገባ ጉዳይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 351/3/ ከጉምሩክ አዋጅ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅና የገቢ ግብር አዋጅ በተለየ ሁኔታ በመንግሥት የገቢ ምንጮች ጉዳት ለማድረስ የተፈጸመው የወንጀል ድርጊት ራሱን የቻለ ሌላ ወንጀል መፈጸሙ የሚያሳይ ከሆነ ሌሎች የሕግ ድንጋጌዎች በተደራቢነት ተፈፃሚ እንደሚሆኑ አመልክቷል፡፡ የሐሰተኛ ወይም የፈጠራ ሂሣብ የማዘጋጀት ድርጊቱ የማታለል ወንጀል ወይም ሐሰተኛ ወንጀል የመፍጠር ወንጀልን ያስከተለ ከሆነ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 378፣692 ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 699 በተመሳሳይ ማናቸውም አይነት የማታለል ተግባር የተፈጸመው ወደ ሐሰተኛነት በተለወጠ ሰነድ አማካይነት ሲሆን አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች በተደራቢነት ተፈፃሚ እንደሚሆኑ ተደንግጓል፡፡ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው ሌሎች አዋጆች ማለትም የገቢ ግብር፣ ተጨማሪ እሴት ታክስ፣ የጉምሩክ አዋጅ ስለዚህ ጉዳይ በዝምታ አልፈውታል፡፡ ስለሆነም ዓቃቤ ሕግ ከወንጀል ሕግ ይልቅ አዋጆቹን ጠቅሶ ክስ የሚያቀርብ ከሆነ የማታለል ወይም ሐሰተኛ ሰነድ መገኘቱ

በተደራቢነት የመክሰስ ሥልጣን ስለመኖሩና አለመኖሩ የተገለፀ ነገር የለም፡፡ ይህ ደግሞ በተከሣሽ ላይ የቀረበው ክስ ከማክበድና ማቅለል አንፃር የራሱ ትርጉም አለው፡፡

2.2.7 ኬላ መስበር/ኮንትሮባንድ/

በዚህ ጽሑፍ ምዕራፍ አንድ መንግሥት በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጽሙ ወንጀሎች ለምን መቆጣጠር አስፈለገ የምለው ጥያቄ የሚመለስ አጭር ቅኝት አድረገናል፡፡ መንግሥት ገቢ የሚሰበስበው ፈርጅ ቡዙ የልማት ሥራዎች ለመሥራት መሆኑ ተመልክተናል፡፡ ይሁንና መንግሥት የጉምሩክ አዋጅ ያወጣበት የፖሊሲ ምክንያት ገቢ ለመሰብሰብ ብቻ አለመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 622/2001 መግቢያ በቀላሉ መረዳት ይቻላል፡፡ የጉምሩክ አዋጅ ለማውጣት እንደመነሻ የተወሰዱ የፖሊሲ ምክንያቶች ስድስት ናቸው፡፡ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ የንግድ ሥርዓት በዓለም አቀፍ ካለው የንግድ እንቅስቃሴ የተጣጣመ ለማድረግ አዋጅ ማስፈለጉ ነው፡፡ ሁለተኛው ምክንያት የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ለማበረታታት ነው፡፡ ይህ ማለት ከቀረጥ ነፃ ሆኖው የሚገቡ ወይም ቅናሽ የሚደረግላቸው ዕቃዎች የኢንቨስትመንት ዘርፎች በመለየት በፖሊሲና የሕግ ማዕቀፍ የተደገፈ ውሣኔ ለመስጠት ያስችላል፡፡ ሶስተኛው ምክንያት ከአሁን በፊት የነበረው የጉምሩክ ሥርዓት ዘመኑ ከሚጠይቀው የንግድ እንቅስቃሴ የማይራመድ በመሆኑ ቀልጣፋና ዘመናዊ ሥርዓት መፍጠር ነው፡፡ አራተኛው ምክንያት የኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ከአለም አቀፍና አሕጉራዊ ስምምነቶች የተጣጣመ ሕግ በማስፈለጉ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የዓለም የንግድ ድርጅት አባል ለመሆን በሂደት ትገኛለች፡፡ ለወደፊቱ የአለም የንግድ ድርጅት (WTO) አባል ስንሆን የንግድ ሥርዓታችን በተለይም የጉምሩክ ሕጐች ከሌሎች አገሮች ሕጐች የተቀራረበና የተጣጣመ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡

ኢትዮጵያ በአፍሪካ የተለያየ አካባቢያዊ የልማት ትስስር ድርጅቶች አባል ናት፡፡ ለምሣሌ የኮሜሣ እና ኢጋድ ማንሳት ይቻላል፡፡ የኮሜሳ አባል አገራት ወደ ኢኮኖሚ ውሕደት የሚያመሩ ከሆነ ወጥ የሆነ የቀረጥና ታክስ ሥርዓት ይኖራቸል፡፡ በአባል አገራት መካከል የሚደረገውን የንግድ ግንኙነት በተለይም ከጉምሩክ ሥርዓት በተያያዘ የጋራ ስምምነት ከሌለ አፈፃፀሙ ሊያስቸግር ይችላል፡፡ የአንድ ዕቃ ስሪት አገር ለመወሰን (Country of 0rigin of goods) ተቀራራቢ መለክያ ከሌለ፣ የሚከለክሉ ወይም ገደብ የሚደረግባቸው ዕቃዎች ለመወሰን የአባል አገራት ስምምነት አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ ጥር 26/1953 የተመሠረተውን የዓለም አቀፍ የጉምሩክ

ድርጅት (WCO) አባል ናት፡፡ የጉምሩክ አዋጁም የቀረጥና ታክስ ሥርዓቱ አለም አቀፍ መርሆዎች ያካተት ነው፡፡፡ በተለይም የታሪፍ አመዳደብ (HS) ሥርዓት መጥቀስ ይቻላል፡፡ አለም አቀፍ የጉምሩክ ድርጅት (WCO) እንደመርህ ከሚወስዳቸው ነጥቦች መካከል ገቢ መሰብሰብ፣ ብሄራዊ ደሕንነት ማረጋገጥ፣ የንግድ ሥራ ማቀላጠፍ፣ ማሕበረሰቡን ከአደጋ መከላከል እና የንግድ ስታትስትክስ ሥርዓት መዘርጋት ነው፡፡ ድርጅቱ እንደግብ የወሰደው አባል አገራት ውጤታማና ስኬታማ የቀረጥና ታክስ ሥርዓት መዘርጋቱን ማረጋገጥ ነው፡፡ በመሆኑም የጉምሩክ አዋጅ ኢትዮጵያ ከፈረመቻቸው አለም አቀፍና አሕጉራዊ ስምምነቶች የተጣጣመ ማድረጉ አስፈላጊ መሆኑ ታሳቢ ተደርጓል፡፡ አምስተኛው ምክንያት የሕዝብ ጤና ሰላምና ፀጥታ የሚያስከበር የሕግ ማስከበሪያ ሥርዓት መዘርጋት ነው፡፡ የንግድ እንቅስቃሴው በአግባቡ የሚመራና የሚቆጣጠር ሥርዓት ካለበተጀለት ለጤና ጉጂ የሆነ ደረጃቸው ዝቅ ያለ የምግብ ፍጆታዎች ፤ የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ፣ አደንዛዥ ዕፅ ፣ ሕገወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውር ሊኖር ይችላል፡፡ በመሆኑም መንግስት ሕግና ሥርዓት የማስከበር ቀዳሚ ሚናውን ለመወጣት የሕግ ማዕቀፍ አስፈላጊ ነው፡፡

የመጨረሻውና ከዚህ ርዕስ በተያያዘ የተቀመጠው የፖሊሲ ምክንያት ኮንትሮ ባንድና ሌሎች የማጭበርበር ወንጀሎች የመከላከል ጉዳይ ነው፡፡ በአዋጅ መግቢያ በግልጽ እንደተቀመጠው የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴ በሕጋዊ የንግድ እንቅስቃሴ በሕዝብ ደህንነት ፣ በመንግስት ገቢና በሌሎችም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገቶች ላይ የሚያስከትሉትን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ ለመከላከል የተጠናከረ የሕግ ማስከበሪያ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ የመሆኑ ጉዳይ ነው፡፡ የኮንትሮባንድ ድርጊት በመንግሥት ገቢ ላይ ከፍተኛ ተጽኖ ያስከትላል፡፡ ይሁንና የኢትዮጵያ መንግስት የጉምሩክ አዋጅ ያወጣበት ምክንያት ገቢ ለመስብሰብ ብቻ ሣይሆን ዘረፋ ቡዙ ተግባራት ለማከናወን ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በሥልጣኔ ቁንጮ የተቀመጡት እንደ አሜሪካ ያሉ አገሮች የጉምሩክ ሕግ የሚታወጀው ገቢ የመሰብሰብ ዓላማን ለማስፈፀም ነበር፡፡ ለምሣሌ በ1835 ዓ/ም የአሜሪካን አገራዊ ወጪ ሙሉ በሙሉ የተሸፈነው ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ መሆኑ የታሪክ መዛግብት ያወሳሉ፡፡ ይሁንና የበለፀጉ አገሮች በጊዜ ሂደት የጉምሩክ ሕግ ዓለማ ገቢ ከማስገኘት ይልቅ በጽረ - ዕፅንግድና ፈጣን የንግድ አገልግሎት በመስጠት ላይ ብቻ እያተኮረ ይገኛል፡፡ ምክንያቱም የገቢ ዋነኛ ምንጭ የካምፓኒዎች የገቢ ግብር ወደ መሆን ተሻግሮዋል፡፡

በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ግን የጉምሩክ ዋነኛ አላማ ገቢ መሰብሰብ ነው፡፡ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ሲንመለከተው ከአጠቃላይ አገራዊ ግብር ገቢ 50 % ከጉምሩክ ገቢ የሚገኝ መሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም የኮንትሮባንድ ድርጊት የመቀነስ በሂደትም የማቆም ሥራ ወሳኝ መሆኑ መገንዘብ አያዳግትም፡፡

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 352 እና የጉምሩክ አዋጅ አንቀጽ 91 ስለኮንትሮባንድ ወንጀል ስያሜ ፣ የማቋቋሚያ ፍሬ ነገርና ቅጣት ደንግጓል፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 352/1/ እና /2/ ዝርዝር ጽንስ ሐሳቦች አካቷል፡፡ አንቀጽ 352/1/ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ "ማንም ሰው አስቦ በሕግ የተወሰነው ቀረጥ ወይም ግብር ያልተከፈለበት ማናቸውም ዓይነት የንግድ ዕቃ ንብረት ፣ ልዩ ፣ ልዩ ዕቃ ወይም የፋብሪካ የእጅ ጥበብ ሥራ የሚያፈራውን ማናቸውንም ዓይነት ነገር ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር ያስወጣ ወይም ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ ያስገባ " የኮንትሮባንድ ድርጊት ነው በማለት ደንግጓል፡፡ በኮንትሮባንድ ድርጊት የሚጠይቁ ግለሰቦች ራሳቸው ድርጊቱን የፈፀሙ ወይም በሕገ ወጥ መንገድ ወደ አገር ውስጥ መግባታቸው እያወቁ ይህንን ዕቃ ያከማቹ ለሺያጭ ያቀረበ ወይም የገዛ ወይም በአገር ውስጥ ተመርተው ቀረጥ ሳይከፈልባቸው እንዳይዘዋወሩ የተከለከሉ ዕቃዎች ወይም ምርቶች ማዘዋወር የወንጀል ተጠያቂነት ያስከትላሉ፡፡ ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 352/1/ሀ/ እና /ለ/ የምናገናዝብባቸው መሰረታዊ ነጥቦች የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበት ዕቃ አስቦ ወደ ኢትዮጵያ ማስገባት ከአገር ማስወጣት የተረጋገጠበት ኮንትሮባንድስት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ሁለተኛው ነጥብ እያወቀ ያስቀመጠ የገዛ ያዘዋወረ ተጠያቂ መሆኑ ነው፡፡ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 352/1/ሀ/ እና /ለ/ መሰረት የኮንትሮባንድ ወንጀል ሆነ ብሎ ወይም አውቆ የሚፈፅም መሆኑ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የቸልተኝነት ድርጊት መሆኑ ከተረጋገጠ በኮንትሮባንድ የሚጠየቅበት ሥርዓት አይኖርም፡፡

የወንጀል ድርጊቱ በግለሰብ ወይም በተደራጀ ቡድን ሊፈፀም ይችላል፡፡ በሌላ በኩል በኃይል፣ በዛቻ በማጭበርበር የተፈፀመ ከሆነ በቅጣት አወሳሰን ረገድ የሚከብድ መሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 352/2/ ተመልክቷል፡፡ የወንጀል ሕግ የሶስተኛ ወገኖች መብት ጠብቀዋል፡፡ የኮንትሮባድን ውጤት የሆነ ንብረት ለመንግስት ሊወረስ ይገባል፡፡ ይሁንና በቅን ልቡና ለወንጀሉ ባዕድ የሆኑት ሰዎች መብት አይነካም፡፡ ለምሣሌ አንድ ሰው የቤት መኪናው ለጓደኛው ለሰርግ ዓላማ ከሰጠው ጓደኛው ድሬዳዋ ለሰርግ ደርሶ መልስ ሲመለስ የኮንትሮባንድ ንብረት ጭኖ ከተያዘ በቅን ልቡና ንብረት የሰጠው ሰው

ንብረት ሊወረስ አይገባም። የወንጀል ሕግ ሌላ ያስቀመጠው መሰረታዊ ነጥብ በጉምሩክ ውስጥ ለጊዜው ብቻ በድንገት የሚፈፀሙ የደንብ መተላለፍ ተግባሮች መደበኛ የወንጀል ተጠያቂነት የማያስከትሉ መሆናቸው ነው። ይልቁንም ስለደንብ ተላላፊዎች በአንቀጽ 784 የተደነገገው ተፈፃሚ ይሆናል። የወንጀል ሕግ ዋና ወንጀል ፈፃሚዎችና የኮንትሮባንድ ድርጊት የመፈፀም አሳብም ሆነ ፍላጐት የሌላቸው ሰዎች ለይቶ ለመቅጣት ያሰበ ይመስላል። የወንጀል ሕግ የኮንትሮባንድ ድርጊት የፈፀሙ ሰዎች እንደ ወንጀሉ አፈፃፀም ከአሥር ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮና በቀላል እስራት አፈጻፀም ከባድ ከሆነ ደግሞ ከአሥር ዓመት በማይበለጥ ጽኑ እስራት ያስቀጣል።

የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 በተመሳሳይ መንገድ የወንጀል ስያሜ፣ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች እና ቅጣት ደንግጓል። ይሁንና ከወንጀል ሕግ መሰረታዊ ልዩነት የሚያሳይ ነገሮች ማካተት ግን ሁለቱም ሕጐች በማንበብ በቀላሉ መረዳት ይቻላል። የወንጀል ሕግ ሌሎች ሕጐች አያጣቅስም። የጉምሩክ አዋጅ በአንፃሩ ደንብና መመሪያ መተላለፍ በተጨማሪ የሚያስጠይቅ መሆኑ ነው። በሌላ በኩል የወንጀል አፈፃፀሙ በተለይም የመሸሸግ ወንጀል የሚፈፅሙ ሰዎች እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው በማለት የተደነገገ ሲሆን የወንጀል ሕግ ግን "እያወቀ " በማለት መደንገጉ በአተረጓጐም ረገድ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል። ሌላ መሰረታዊ ልዩነቱ አዋጁን ተላልፈው የተገኙ ሰዎች የሚጣልባቸው ቅጣት ነው። እንደ ወንጀሉ አፈፃፀም ከ7--15 ዓመት ወይም ኃይል በመጠቀም ወይም በቡድን ከሆነ 15-20 ዓመት ያስቀጣል።

ከኮንትሮባንድ ወንጀል በተያያዘ በርካታ ነገሮች ይነሳሉ። የመጀመሪያው በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 የሰፈረው የወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር "ማንም ሰው ይህንን አዋጅ ወይም ባለስልጣኑ የሚያስፈጽማቸው ሌሎች ሕጐች ወይም በነዚሁ መሰረት የወጡ ደንቦች መመሪያዎች መተላለፍ " የሚለው አገላለጽ የኮንትሮባንድ ወንጀል ለማቋቋም በቂ ናቸው ወይስ አይደለም የሚል ነው። ሁለተኛው የክርክር ነጥብ የጉምሩክ ወንጀል በተለይም ኮንትሮባንድ ወንጀል ፍፃሜ ያገኘና ያላገኘ ተብሎ ሊከፈል ይችላል ወይስ አይችልም የሚል ነው። ሶስተኛው የክርክር ነጥብ የገንዘብ መቀጮ በተመለከተ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር የሚመጣጠን መሆን አለበት ሲባል እኩል መሆን አለበት ማለት ነው? ወይም ዳኞች ነባራዊ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ አስገብተው የሚወስኑት ነው ? ዳኞች የገንዘብ መቀጮ ማቅለል ይችላሉ? አራተኛውና የመጨረሻው የክርክር ነጥብ በወንጀል ሕጉና በጉምሩክ አዋጅ

ቁጥር 622/2001 የተደነገገው ቅጣት ስንመለከተው በወንጀል ሕጉ መነሻና መድረሻ ቅጣቱ አነስተኛ ሲሆን በጉምሩክ አዋጅ ደግሞ ከወንጀል ሕጉ አንፃር ሲታይ ከብዶ የተደነገገ በመሆኑ በወንጀል ሕጉና በልዩ ሕጉ (የጉምሩክ አዋጅ) ያለውን ልዩነት ለማጣጣም የትኛው ሕግ ተፈፃሚ መሆን አለበት የሚሉ ናቸው፡፡ የፌደራል ፍ/ቤቶች ሰበር ችሎት ጭምር አንዳንድ ጉዳዬች ላይ አቋም የወሰዱባቸው በመሆኑ በተወሰነ መልኩ ለመዳሰስ ጥረት ይደረጋል፡፡ የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ዳኞችና ዓቃቢ ሕጐች በተግባር እያጋጠሙ ያሉ ችግሮች መሰረት በማድረግ የሕጉ መንፈስና ዓላማ ተከትለው እንዲተረጉሙት ነው፡፡

የመጀመሪያው ነጥብ በተመለከተ ደንቦችና መመሪያዎች መተላለፍ የወንጀል ተጠያቂነት ያስከትላልን የሚል ነው፡፡ የዚህ ክርክር ጭብጦች ለሁለት የተከፈሉ ናቸው የመጀመሪያው የክርክር መስመር ሕግ አውጪው አስፈፃሚው ደንቦችና መመሪያዎች እንዲወጣና እንዲያስፈፅም ውክልና ከተሰጠው የወንጀል ተጠያቂነት ማስከተላቸው ሕግን የሚቃረን አይደለም የሚል ነው፡፡ ይህንን የክርክር መስመር በተመለከተ በፌደራል ፍ/ቤቱ የተለያየ አቋም የተያዘበት ሲሆን በሰበር ሰሚ ችሎት የመጨረሻ መቋጫ አግኝቷል፡፡ የሰበር መዝገብ ቁጥር 43781 ሐምሌ 14 ቀን 2002 (በቅጽ 10 ገጽ 388 - 392 ይመለከተዋል) በተሰጠው ውሳኔ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተከሣሹ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 60/89 በአዋጅ ቁጥር 368/95 እንደተሻሻለው አንቀጽ 2/28/ እና አንቀጽ 66/2/ በመተላለፍ የኮንትሮባንድ ወንጀል ፈጽሟል በማለት የመጀመሪያ ክስ፤ በአማራጭነት ደግሞ የባንክ አዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 59/2/ለ/ ሥር የተጠቀሱና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ስለወርቅ ግብይት ቁጥጥር ያወጣውን መመሪያ ቁጥር CTG 1001/97 አንቀጽ እና 2 በመተላለፍ በሕገወጥ መንገድ ወርቅ ሲያዘዋውር በአገር ኢኮኖሚ ላይ ከባድ ጉዳት አድርሷል የሚል ነበር፡፡ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአማራጭ በቀረበው ክስ ጥፋተኛ በማለት በአምስት ዓመት ጽኑ እስራትና አንድ ሚሊዮን ብር መቀጮ እንዲሁም የተያዘው ወርቅ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ወስኗል፡፡

በይግባኝ የተመለከተው የፌደራል የከፍተኛ ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ በመሻር ተከሣሹ በነፃ እንዲሰናበት ወስኗል፡፡ ፍ/ቤቱ በፃፈው ሐተታ መመሪያ ቁጥር 001/97 ሕግ ሆኖ አስገዳጅነት እንዲኖረው በአዋጅ ቁጥር 3/87 እና 14/88 መሰረት በነጋሪት ጋዜጣ "ታትሞ ያልወጣ እንዲሁም በአማረኛ ቋንቋ ያልተፃፈ በመሆኑ ሕግ

ሆኖ ቅጣት ሊጥል አይችልም በወንጀል ተጠያቂ ሊያሰኝ አይችልም" የሚል ነው፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ተመሳሳይ አቋም ወስዷል፡፡ የሰበር ሰሚ ችሎት የሥር ፍ/ቤቶች /የከፍተኛና ጠቅላይ / በመሻር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔ አጽንቷል፡፡ ብሄራዊ ባንክ ያወጣው መመሪያ በአማረኛ ቋንቋ ያልተፃፈ መሆኑ በነጋሪት ጋዜጣ አለመታተሙ ሕግ ከመሆን የሚያስቀረው አለመሆኑ የወንጀል ተጠያቂነትም በአዋጁ መሰረት የተደነገገ መሆኑ ታሳቢ ያደረገ መሆኑ ከውሣኔው መረዳት ይቻላል፡፡ የሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ትርጉም አስገዳጅ በመሆኑ በአስፈፃሚ የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የወንጀል ተጠያቂነት ያስከትላሉ የሚል አቋም የሚደግፍ ነው፡፡

ሁለቱኛው የክርክር ጭብጥ ከዚህ በተቃራኒ የሚቆም ነው፡፡ የክርክሩ ዋና ጭብጦች በዚህ ጽሑፍ በ2.1 ሥር ስለአጠቃላይ ድንጋጌዎች ሲነሳ የተነሱ ነጥቦች የሚያጠናክር ነው፡፡ አንደኛው የሕግ አወጣጥ ሥርዓት በተመለከተ ወንጀል የመደንገግ ሥልጣን የሕዝብ ተወካዩች ም/ቤት መሆኑ ነው፡፡ የሕዝብ ተወካዩች ም/ቤት ወንጀል ሕግ ያወጣል ሲባል የወንጀሉ ስያሜ፣ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች እና የቅጣት መጠንና ዓይነት ያስቀምጣል ማለት ነው፡፡ አስፈፃሚው ደንብና መመሪያ በማውጣት የወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች የሚወስን ከሆነ የሰብአዊ መብት አጠባበቅ ሥርዓት ችግር ሊኖር ይችላል፡፡ ከአፈፃፀም አንፃር ደንቦችና መመሪያዎች ከአዋጅ በኋላ የሚወጡ በመሆናቸው ወደ ኃላ ተመልሰው የመፈፀም ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ በምሣሌ ለማስደገፍ ብሄራዊ ባንክ በ2003 አንድ ሰው አንድ ሺህ ብር ከአገር ይዞ ሲወጣ ከተያዘ የኮንትሮባንድ ወንጀል እንደፈፀመ ይቆጣጠራል በማለት መመሪያ ካወጣውና በ2004 ካሻሻለው ማለትም ወደ ሁለት ሺህ ብር ከፍ ካደረገው ሕጉ ወደ ኃላ ተመልሶ ተፈፃሚ ከመሆኑ በተጨማሪ የወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር የመደንገግ ያህል ነው፡፡ ሁለተኛው የመከራከሪያ ነጥብ አዋጅ ፣ ደንብና መመሪያ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ካልወጣ ሕዝቡ እንዴት ማወቅና ማግኘት ይችላል፡፡ በሶስተኛ ደረጃ የደንብና መመሪያ ዓላማ አዋጅን ማስፈፀም ከሆነ መደበኛ የወንጀል ተጠያቂነት ማስከተሉ በመደበኛ የወንጀል ተጠያቂነት እና የደንብ መተላለፍ ተጠያቂነት የመደበላለቅ ችግር ይፈጠራል ፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 የተቀመጠው አገላለጽ ከወንጀል ሕግ መደንገግ አንፃር ተገቢ አይደለም በማለት ይከራከራሉ፡፡

ጥያቄ   እርስዎ የተኛው የአተረጓጎም መስመር ይደግፋሉ ለምን?

ሌላው አከራካሪ ነጥብ የሆነው የጉምሪክ በተለይም የኮንትሮባንድ ወንጀል ፍፃሜ አገኘ የምንለው መቼ ነው? በሌላ አገላለፅ የኮንትሮባንድ ወንጀል በሙከራ ደረጃ ቀረ ወይም ሙከራ ነው ለማለት ይቻላልን ? የሚል ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ መነሻ የሆነው የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና ከፍተኛ ፍ/ቤት በአንድ በኮንትሮባንድ በተያዘው ጉዳይ የሰጡት የተለያየ ትርጉም ነው፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ.መ.ቁ.176034 ሐምሌ 4 ቀን 2003 በሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በመቃወም ዓ/ሕግ ይግባኝ በመጠየቁ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት በተከሣሽ ፋጡማ ዐሊ ዓ/ሕግ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 በመጥቀስ ያቀረበው ክስ ተከሣሿ ከኢትዮጵያ በቦሌ አየር ሪፖርት በኩል ወደ ኬንያ አገር ሲትወጣ መጠኑ 1954.15 ግራም ወርቅ የቀረጥና ታክስ መጠኑ 912657.90 በሆነ በኤክስሬይ ማሽንና በአካል በተደረገ ፍተሻ መያዙ ያትታል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ወንጀሉ በሙከራ ደረጃ የቀረ በመሆኑ ከመነሻው በመውረድ የ5 ዓመት እስራትና አንድ መቶ ሃያ አምስት ሺህ ብር መቀጮ ወስኗል፡፡ የመቀጮው ጉዳይ ለይተን የምንመለከተው በመሆኑ ለጊዜው አቆይተን ስለወንጀል ሙከራ መሆኑና አለመሆኑን እንመልከት፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ በኮ.መ.ቁ. 112268 ሕዳር 01/2004 በሰጠው ውሣኔ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ሽሮታል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በሰጠው ሐተታ ለክሱ መነሻ የሆኑ ወርቆች ወደ ጉምሩክ ክልል በተጨባጭ ገብተው እጅ ከፍንጅ የተያዙበት ሁኔታ መሆኑ በመረጋገጡ ፍፃሜ ያገኙ ወንጀል ነው በማለት ወሰኗል፡፡

የኮንትሮባንድ ወንጀል ምን ማለት እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 ላይ እንደተመለከትነው የተከለከሉ ፣ ገደብ የተደረገባቸው ወይም የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመባቸው ዕቃዎች ማስገባት ፣ ማስወጣት ፣ በሕጋዊ መንገድ የወጡ ዕቃዎች በሕገወጥ መንገድ ያስገባ ከሆነ የኮንትሮባንድ ወንጀል መፈፀሙ ያሳያል፡፡ በመርህ ደረጃ አንድ የወንጀል ድርጊት ፍፃሜ ያገኘ እና ያላገኘ በማለት መክፈሉ ተገቢ ነው፡፡ ይሁንና ከኮንትሮባንድ ጋር በተያያዘ ግን በጥንያቄ መታየት አለበት፡፡ አንድ ሰው የጉምርክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀሙት እቃ ይዞ ከተገኘ የወንጀል ድርጊቱ ፍፃሜ አላገኘም ለማለት አስቸጋሪ ነው፡፡ በሌላ በኩል የኮንትሮባንድ ወንጀል ባሕሪ ታሳቢ ካለተደረገ በተለይም ከኢትዮጵያ የግዛት ክልል ከወጣ በኂላስ መንግስት ክስ በማቅረብ ወንጀለኞች ማስቀጣትና ግብርና ታክስ መሰብሰብ ይቻላል ወይ

ጥያቄ የሚያስነሣ ነው፡፡ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 2/36/ ፣ 2/42/ ስለጉምሩክ ወደብና፣ የጉምሩክ ጠረፍ መስመር ትርጓሜ ሰጥቷል፡፡ የጉምሩክ ወደብ ማለት ለጉምሩክ ሕግ አፈፃፀም ሲባል የገቢ፣ የውጪና የተላላፊ ዕቃዎች የሚራገፍበት የሚቆዩበትና የሚጫኑበት በባለ ሥልጣኑ የሚወሰን ማናቸውም ስፍራ ሲሆን ደረቅ ወደብ እንደሚጨምር ፤ የጉምሩክ ጠረፍ መስመር ማለት ደግሞ ከኢትዮጵያ የጉምሩክ ደንበር መስመር ወደ ውስጥ እስከ 15 ሜትር ገባ ብሎ የሚገኝ ሥፍራ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ አዋጅ ትርጓሜ መገንዘብ የሚቻለው ኮንትሮባንድ ወንጀል ለመባል ዕቃው ከአገር መውጣት ወይም የመጨረሻ የደንበር መስመር መሻገር አለበት ማለት አለመሆኑን ልብ ይለዋል፡፡

ሶስተኛው የክርክር ነጥብ ከመቀጮ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የኮንትሮባንድ ድርጊት በመፈፀም ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘው ሰው መቀጮ በተመለከተ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር የሚመጣጠን መሆን አለበት ማለት እኩል መሆን አለበት ማለት ነው ? ዳኞች ግምት ውስጥ የሚያስገቡት ነገር የለም ማለት ነው? ዳኞችስ የእስራት ቅጣት ማቅለል እንደሚችሉ ሁሉ መቀጮስ ማቅለል ይችላሉ? የሚሉ ጥያቄዎች ያከራክራሉ፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ.መ.ቁ. 176034 መቀጮ በማቅለል በመወሰኑ የገቢዎችንና ጉምሩክ ባለስልጣን ዓ/ሕግ ይግባኝ በመጠየቁ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ.መ.ቁ. 112268 በመሻር ወስኗል፡፡ ፍ/ቤቱ ውሣኔውን ለመሻር በሰጠው ምክንያት " መቀጮ በተመለከተ ሕጉ ከቀረጥና ከታክሱ ጋር የሚመጣጠን ብሎ ዘግቶታል መነሻ የገንዘብ መቀጮ የቀረጥና ታክሱ መጠን ነው በወ/ሕ/አንቀጽ 179 ሥር የገንዘብ መቀጮው መነሻ ሕግ አውጪው መሸርሸር ቢፈልግ በግልጽ የመቀጮ መነሻው ከፍ ያለውን መቀነስ ይቻላል ይል ነበር መነሻ መቀጮው ከፍ ካለ አስገዳጅ ቅጣት " --- ነው በማለት ወስኗል፡፡

የኮንትሮባንድ ወንጀል ከባድ ወንጀሎች ተብለው ከሚመደቡት አንዱ ነው፡፡ የቅጣት መነሻውም ከፍ እንዲል የተደረገበት ምክንያት የኮንትሮባድን ወንጀል ለመከላከል ካለው ፋይዳ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ መቀጮ በተመለከተም ወንጀል ፈፃሚዎች ሊከፍል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር በሚመጣጠን (afine equivalent) ሊቀጡ እንደሚገባው ተደንግጓል ፡፡ ዳኞች ይህንን አስገዳጅ ደንጋጌ በመሸርሸር አስተያየት ማድረግ ወይም ምሕረት የመስጠት ሥልጣን የላቸውም፡፡ ወንጀል ፈፃሚዎች ተገቢው ቅጣት ተወስኖባቸው ከኮንትሮባንድ ድርጊት ሙሉ በሙሉ እንዲወጡ ማድረግ ተገቢ

ነው፡፡ ይህንን ካልሆነ በአዋጅ መግቢያ የተቀመጡ የፖሊሲ ምክንያቶች ማሳካት አይቻልም፡፡ ምናልባት የመቀጮው መጠን ከፍተኛ መሆኑ የአመክሮ ውሣኔ በመስጠት ረገድ ተጽኖ ሊኖረው ይችላል፡፡ ይሁንና ሕግ አውጪው የመቀጮ ቅጣት ከፍ ማድረጉ ሲታይ የአመክሮ ጉዳይ አልተመለከተውም ነበር ለማት አልተቻለም፡፡ ያም ሆነ ይህ የአመክሮ ጉዳይ ዳኞች ከመቀጮው አንፃር ያለው አንደምታ እንደጉዳዩ አመጣጥ ለመወሰን ይችሉ እንደሆነ እንጂ ለአመክሮ ዓላማ ተብሎ ዳኞች በአስተያየት ወደ መወሰን መሄድ አይገባቸውም፡፡

ዳኞች የገንዘብ መቀጮ ማቅለል ይችላሉ ወይስ አይችሉም የሚል ክርክር መፍትሄ ያገኘ ጉዳይ አይደለም፡፡ በዚህ ዙሪያ ሁለት የክርክር መስመሮች ይራመዳሉ፡፡ የመጀመሪያ የክርክር መስመር የፌደራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት የተከተለው የአተረጓጎም ሥርዓት ነው፡፡ አንዳንድ ዳኞች መቀጮ እንደማንኛውም ቅጣት ማቅለል እንደሚቻል ይገልጻሉ፡፡ ለዚህ እደመነሻ የሚወሰደው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 90/2/ ዳኞች መቀጮ ሲወስኑ የሀብት ሁኔታ ፣ የገቢው መጠን..... ወዘተ ግምት ውስጥ ማስገባት እንዳልባቸው ተመልክቷል፡፡ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 91 ፍ/ቤት መቀጮውና እስራት ማጣመር መቀጮ በሥራ መለወጥ እንደሚቻል መደንገጉ ፍ/ቤት መቀጮ ማቅለል ወይም ነፃ ማድረግ ይችላል በማለት ይከራከራሉ፡፡ ከዚህ በተቃራኒ የሚከራከሩት ባለሙያዎች ፍ/ቤቶች መነሻው የታወቀ መቀጮ መቀነስ አይችሉም የሚል ነው፡፡ ለዚህ እንደ መነሻ የሚወሰደው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 179 ፍንጭ የማይሰጥ መሆኑ ነው፡፡ የወንጀል ሕግ አንዳንድ ድንጋጌዎች ፍ/ቤቶች እስራትን በተመለከተ ማቅለል እንደሚችሉ የደነገጉ ቢሆንም ስለመቀጮ ግን በግልጽ የተደነገገ ነገር የለም፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 180 መሰረት በማድረግ ፍ/ቤት በመሰለው ቅጣት ማቅለል እንደሚቻል፤ ይሁንና ፍ/ቤት በመሰለው ቅጣት ለማቅለል እንደሚችል በሕግ በግለጽ መደንገግ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ ፍ/ቤቱ በሕግ በግልጽ በተደነገገ ጊዜ በመሰለው ቅጣት ማቅለል ቢችልም መነሻው ግን ዝቅ ማድረግ እንደማይችል ተመልክቷል፡፡ /አንቀጽ 90፣106 እና 108 ይመልከቱ/፡፡ በዚህ ሕግ አንቀጽ ሥር መቀጮ ማቅለል እንደሚቻል ፍንጭ የሚሰጥ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ቅጣት በመሰለው ለማቅለል በሕግ በግልጽ በተፈቀደ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ የወንጀል ሕጉ ሲንመለከተው ፍ/ቤቱ መቀጮ በተመለከተው በመሰለው ለማቅለል የሚያስችል ነገር ስለመኖሩ አያሳይም፡፡ የወንጀል ሕግ ሐተታ ዘምክንያትም ከዚህ ጋር በተያያዘ ምንም ፍንጭ አይሰጥም፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ መነሻው የታወቀ መቀጮ ዝቅ

በማድረግ የመወሰን ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ ግልጽ አይደለም፡፡ የመቀጮው መነሻ እና መድረሻ በግልጽ ባልተደነገገበት ሁኔታ ፍ/ቤቱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 90/1/ እና /2/ መሰረት በማድረግ መወሰን ይችላል፡፡ ፍ/ቤቶች በመቀጮ አወሳሰን ረገድ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 90/2/ በጥንቃቄ መመርመር ይገባቸዋል፡፡

አራተኛው የመጨረሻው የክርክር ነጥብ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001/ አንቀጽ 91(1) መተላለፍ ከ7-5 ዓመት ያስቀጣል፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 352 ሥር የተደነገገው ቅጣት ከብዶ የሚወሰን ቢሆን እንኳ ከአሥር ዓመት የማይበልጥ ነው፡፡ ሁለቱም ሕጎች ስንመለከታቸው በአንድ ሕግ አውጪ አካል የወጡ ሲሆኑ የጉምሩክ ሕግ ሊያሳካ ካሰበው ዓላማ አንፃር እንደልዩ ሕግ የሚታይ በመሆኑ ተፈፃሚነት ሊኖረው ይገባል የሚል ክርክር ይነሳል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሁለቱም የወንጀል ድንጋጌዎች ተመሳሳይ የወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬነገርና ስያሜ ኑሮዋቸው የተለያየ የቅጣት መነሻና መድረሻ የያዙ ከሆኑ ተከሳሹን የሚጠቅመው ሕግ ተፈፃሚ ማድረግ አለብን ብለው የሚከራከሩ የሕግ ባለሙያዎች አሉ፡፡

- ***<u>የመወያያ ጥያቄ</u>***
  1. እርስዎም እንደ ዓቃቤሕግና ዳኛ ሲሰሩ የትኛው የአተረጓጎም መንገድ ሲከተሉ ነበር ?
  2. በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 የኮንትሮባንድ ወንጀል መፈጸምና በአንቀጽ 99 ሕገወጥ ዕቃዎች ይዞ መገኘት አንድነቱና ልዩነቱ ምንድነው?
  3. አንድ የመኪና ሹፌር እና ረዳቱ የኮንትሮባንድ ንብረት ጭነው ከተገኙ በእኩል ደረጃ ኃላፊ ሊሆኑ ይገባል ወይስ አይገባም? ለምን?
  4. የወንጀል ሕጉና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/200/ አንዳንድ ድንጋጌዎች እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ወይም በቸልተኝነት የተፈጸመ እንደሆነ በማለት እንደ ማቋቋሚያ ፍሬነገር ያስቀምጣሉ፡፡ ለመሆኑ ማወቅ ሲገባው የሚለው ፍሬነገር መስፈርቱ እንደየሁኔታው የሚታይ (Subjective standard) ነው ወይስ የአንድ ምክንያታዊ ሰው መመዘኛ (መስፈርት) (objective standard) መሠረት በማድረግ ነው?የትኛው መመዘኛ ወይም መስፈርት የወንጀል ሕጉና ልዩ ልዩ አዋጆች ዓላማ የሚያሳካ ይመስሉዎታል?ለምን?

2.2.8 በአገር ኢኮኖሚ በመንግስት ምኖፖል ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 353 ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮች ይዞ እናገኘዋለን፡፡ የመጀመሪያው የወንጀል ሕግ ታሳቢ የሚያደረገው ልዩ ሕጐች ነው፡፡ ሁለተኛው ነጥብ ደንብ መተላለፍ ድርጊቶች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 784-790 ባሉት ድንጋጌዎች የሚሸፍን መሆኑ ነው፡፡ ሶስተኛው ነጥብ የወንጀል ድርጊት በቸልተኝነት የተፈፀሙ ከሆነ በቅጣት አወሳሰን ረገድ ግምት ውስጥ የሚገባ መሆኑ ነው፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 353/1/ሀ-ረ/ የዘረዘራቸው ድርጊቶች ልዩ የወንጀል ሕግ መኖሩ ታሳቢ ያደርጋል፡፡ በ "ሀ" ሥር የተመለከተው ከክልከላ ፣ ፍቃድ ቁጥጥር የተያያዘ ነው፡፡ በተለይም ከጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ተያያዥነት አለው፡፡ ምክንያቱም ከአገር ውስጥ ማስወጣትና ማስገባት ይመለከታል፡፡ "ለ" ሥር ደግሞ በተፈጥሮ ሀብት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ "ሐ" ሥር የተመለከተውን በዱር እንሰሳት ፣ /መ/ በተከለከሉ ደኖች ፣ /ሠ/ የመንግስት ምኖፖል /2/ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚመለከቱ ድንጋጌዎች አስቦ የጣሰ በወንጀል ያስጠይቃል በማለት ደንግጓል፡፡ በዚህ ሕግ አንቀጽ /2/ ስለ ጀኔቲክ ሀብት ፣ /3/ ስለብርቅዬ እንሰሳት ይመለከታል፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 353 ተፈፃሚ የሚሆነው በልዩ ድንጋጌዎች ከፍ ያለ ቅጣት ያልተመለከተ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ሕግ አውጪው ከፍ ሲል የተጠቀሰው የወንጀል ድርጊት የሚመለከቱ የተለያዩ አዋጆች ማውጣቱ ግልጽ ነው፡፡

የዱር እንሰሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም በተመለከተ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጀ ፍ/ቤት አራዳ ምድብ ችሎት በርካታ ክሶች ይቀርባሉ፡፡ በተግባር ከታዩ ችግሮች አንዱ በፍ/ቤት የሚወሰኑ ቅጣቶች የወንጀሉ ምንጭ ለማድረቅ የሚያስችሉ አለመሆናቸው ነው፡፡ ምክንያቱም እንሰሳት ከተገደሉ በኃላ አንዳንዴም በዘመቻ የሚደረግ የወንጀል መከላከል ተግባር ግቡን የመታ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በሌላ በኩል የውጭ ዜጐች ሲከሰሱ ከሚያነሱዋቸው ክርክሮች የዝሆን ጥርስ ከውጭ አገር ይዘን የገባን ቢሆንም ተቀጥተናል የሚል ነው፡፡ በአራዳ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ.መ.ቁ. 96023 የተሰጠው ውሣኔ ማየት የቻላል፡፡ በተለይም ቻይናዊያን ለዝሆን ጥርስ ወይም ጌጣጌጥ ያላቸው ፍቅር ለቅጣት እየደረጋቸው መሆኑ ይገልፃሉ፡፡ ፍ/ቤቶች ተከሳሾች ጥፋተኛ ካሉ በኃላ አዘውትረው መቀጮ ሲወስኑ ይታያሉ፡፡ የዱር እንሰሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 አንቀጽ 16 /iii/ የተላለፈ ጥፋኞች በመቀጮ ከብር አምስት ሺ በማያንስና ከብር 30 ሺ መሆኑ የእስራት ቅጣት ደግሞ ከ1 ዓመት

በማያንስ ከ5 ዓመት በማይበልጥ እስራት እንደሚያስቀጣ ተደንግጓል፡፡ አንዳንድ የውጭ አገር ዜጐች ከውጭ አገር የእንስሳት ውጤት የሆነ እቃ ይዘው ሲገቡ የምዝገባ ሥርአት ቢዘረጋ አገር ለመጐብኘት የመጡ ግለሰቦች ያለምንም ስጋት ከአገር ሲወጡ በአግባቡ ማስተናገድ ይቻላል፡፡ ይሁንና ኢትዮጵያ ከእንስሳት ልማት በተያያዘ ዓለም አቀፍ ስምምነት ፈራሚ በመሆኗ የዝሆን ወይም የሌሎች እንስሳት ውጤት ይዘው የተገኙ ሰዎች ከማይከለክል አገር ይዘውት ቢገቡም የወንጀል ተጠያቂነት ሊያስከትል ይችላል፡፡

2.2.9 *1949 ዓ.ም በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በመንግሥቱ የቀረጥና የግብር ገቢዎችና በጠቅላላ የገንዘብ ጥቅሞቹ ላይ ስለሚሠሩ ወንጀሎች አጠቃላይ ድንጋጌዎች አጭር ምልከታ*

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በ1997 ዓ.ም በታወጀው የኢፌድሪ የወንጀል ሕግ ተተክቷል፡፡ የድሮ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ከቁጥር 354-365 አጠቃላይና ዝርዝር ድንጋጌዎች አካቷል፡፡ ሐተታ ዘምክንያት ግልጽ እንዳደረገው አዲሱ የወንጀል ሕግ አሁን ያለው ነባራዊ ሁኔታ ማለትም የኢኮኖሚ፤ ፖለቲካና ማሕበራዊ ሁኔታዎች ታሳቢ በማድረግ በድንጋጌዎቹ ስያሜና የቅጣት መጠን ለውጥ አሳይቷል፡፡ በ1949 ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በሁሉም ድንጋጌዎች ማለት ይቻላል ቀላል እስራት እንደመነሻ የወሰደ ሲሆን መቀጮ በተመለከተም እስከ አሥር ሺህ ብር የሚያስቀጣ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ለምሣሌ የኮንትሮባንድ ወንጀል ከወሰድን እስከ አሥር ሺህ ብር ሊደርስ በሚችል መቀጮ ወይም በእስራት ያስጣል፡፡ የ1949 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የተሻረ ሕግ ነው፡፡ ይሁንና ከ1997 ዓ.ም በፊት የተፈጸሙ የወንጀል ድርጊቶች ካሉና የይርጋ ጊዜ ያላለፈባቸው ከሆነ የክስ አቀራረብና ውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓቱ ምንሊሆን ይችላል የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ የወንጀል ሕግ አጠቃላይ መርሆዎች ስንመለከት እንዲሁም በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 6 የኢፌዲሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ 22(1) ጥምር ንባብ ግልጽ እንደሚያደርገው ለተከሳሹ የተሻለው ሕግ ተፈፃሚ እንደሚሆን ነው፡፡ ይህ ማለት ከ1997 ዓ.ም በፊት የተፈፀመና የይርጋ ጊዜ ያላለፈበት የኮንትሮባንድ ክስ ወይም ተመሳሳይ ክስ የቀረበ እንደሆነ አዲሱ የወንጀል ሕግ ወይም የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ተፈፃሚ አይሆንም ማለት ነው፡፡

ኮንትሮባንድ በተመለከተ በነባር ወንጀል ሕግና አዲሱ የወንጀል ሕግ በቅጣት መነሻና መድረሻ የጐላ ልዩነት ይታያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ከአዲሱ የወንጀል ሕግ በቅጣት መነሻና መድረሻ ከፍ ብሎ ተደንግጓል፡፡

ለዚህ እንመነሻ የሚወሰደው በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በሕዝብ መብትና ጥቅም የሚያደርሱት ጉዳት ከጊዜ ወደ ጊዜ በመጨመሩ ነው፡፡ የወንጀል ድርጊቱ ለመከላከል በሂደት የማክሰም እንቅስቃሴ እውን ሊሆን የሚችለው ሕጐች ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘቡ ሲሆኑ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም አዲሱ የወንጀል ሕጉና የተለያዩ ኢኮኖሚክነክ አዋጆች ከነባሩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በተለየመልኩ ከባድ ቅጣት የመደንገጋቸው ሚስጥር በኢኮኖሚና ገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች መቀነስ ይቻላል ዘንድ ወንጀል ፈፃሚዎች የሚያስተምርና የሚያርም (specific deterrence) ማሕበረሰቡም የሚያስጠነቅቅ (geneneral deterrence) ውጤት ያለው ፍትህ እንዲሰጥ አስፈላጊ በመሆኑ ነው ፡፡ በመሆኑም በነባር የወንጀል ሕግ መሠረት መቅረብ የሚገባቸው የወንጀል ጉዳዮች ካሉ የወንጀል ሕጉ አጠቃላይ መርሆዎች ባስከበረ መልኩ ሊቀርቡ ይገባል፡፡

ምዕራፍ ሶስት

በኢኮኖሚ የገዝብ ጥቅም ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች በተግባር የሚያጋጥሙ ችግሮችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች

3.1 ችግሮች

3.1.1 የወንጀል ሕግና አዋጆች አጣጥሞ ከመተርጐም አንፃር ክፍተቶች የሚታዩ መሆናቸው፣

የወንጀል ሕግ መርሆዎች ምን ያህል ይተገበራሉ?፡፡ የሕገመንግስት አንቀጽ 22 በሚደነግገው አገባብ የተሻለ አማራጭ ከመውሰድ አንፃር ክፍተቶች ይታያሉ፡፡ የደንቦችና መመሪያዎች ዓላማ በተለይ አዋጅ ከማስፈፀም አንፃር የወንጀል ድርጊት የማቋቋም የሕግ ኃይል አላቸው ወይስ የላቸውም የሚል ነጥብም ያከራክራል፡፡ በመሆኑም ዳኞችና ዓቃቢያን ሕግ የወንጀል ሕግ መርሆዎች ከልዩ ወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች /አዋጆች/ አጣጥሞ መተርጐምና መረዳት ያስፈልጋል፡፡

3.1.2. በኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ የተፈፀሙ ወንጀሎች ውስብስብ መሆንና የማስረጃ አሰባሰብ ሥርዓት ደካማ መሆን፣

የኮንትሮባንድ ወንጀል ከባድ ከመሆኑ አንፃር ማስረጃዎች በጥንቃቄ ሊመዘኑ ይገባል፡፡ የውጭ ምንዛሪ በተመለከተም ቤት ከፈተው በስማቸው ንግድ ፈቃድ አውጥተው ሲሠሩ የተገኙ የወንጀል ተሣትፎ የላቸውም በማለት በነፃ ተለቀዋል፡፡ የምርመራ ሥራው እንደ ወንጀሉ አፈፃፀምና ክብደት በጥንያቄ መካሄድ አለበት፡፡ የዱር እንሰሳት ልማት በተመለከተም ከምንጩ የማድረቅ ችግር ይታያል፡፡

3.1.3 ደንቦችና መመሪያዎች ለሕዝቡ ተደራሽ አለመሆናቸው እንደችግር ሊወሰድ የሚችል ነው፡፡ በመሆኑም የመከላከል ሥራ መቅደም ያለበት በመሆኑ ደንቦችና መመሪያዎች ተደራሽ የሚሆኑበት ሥርዓት መዘርጋት ተገቢ ነው፡፡ በብሄራዊ ባንክና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ለተጠቃሚው ማሕበረሰብ ተደራሽ አይደሉም፡፡ በተለይም የውጭ ዜጐች ለኢንቨስትመንት ወይም ለጉብኝት ሲመጡ የሚከሰተው መደናበር ማስቀረት የሚያስችል ሥራ በጥንቃቄ ካልተሰራ የተፈለገው የአገር ገጽታ ግንባታ እና ኢንቨስትመንት ፍሰት ላይገኝ ይችላል፡፡

3.1.4. የአስፈፃመው ተቋማትና የዳኝነት አካል በኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ተጽኖ መቋቋም የሚያስችል አደረጃጀት በተሟላ መልኩ ያልተጠናከረ መሆኑ

በኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅም ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ለመከላከል ለመቅጣት የሚያስችል የሰለጠነ የሰው ኃይል ፣ አደረጃጀት፤ የቴክኖሎጂ አቅርቦት ሊኖር ይገባል፡፡

3.1.5. በኮንትሮባንድ ወንጀል የሚከሰሱ ሰዎች በዋስትና ከተለቀቁ በኃላ የመጥፋት አደጋ ይከሰታል፡፡ በተደራጀ ወይም በቡድን የሚፈፀም የኮንትሮባንድ ወንጀል የተከሰሱ ሰዎች በዋስትና ከወጡ በኃላ ይጠፋሉ፡፡ አንድ ኮንትሮባንዲስት የተያዘ ከሆነ ገንዘብ በማዋጣት በቡድን የዋስትና ቦንድ ካስያዙ በኃላ የመጥፋት አደጋ እያጋጠመ ነው፡፡ ዳኞች እና ዓቃቢያን ሕግ በየጊዜው የሚወጡ አዋጆች ፣ ደንቦችና መመሪያዎችና የፖሊሲ ምክንያቶች ጠንቅቀው ሊረዱት ካልቻሉ ተገቢው ውሣኔ መስጠት አይችሉም፡፡

3.2 <u>የመፍትሄ አቅጣጫዎች</u>

3.2.1. በኢኮኖሚና ገንዘብ ነክ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች የሚመለከቱ ሕጐች ተደራሽ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ዳኞችና ዓቃቢያን ሕግም የአዋጆች ፣ ደንቦች መመሪያዎች የፖሊሲ ምክንያቶች ጠንቀቀው ማወቅና መረዳት አለባቸው፡፡

3.2.2 በኢኮኖሚ የገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ትርጉምና ይዘት ተቀራራቢ መለኪያ ማበጀት ተገቢ ነው፡፡ በምዕራፍ ሁለት እንደተመለከትነው በወንጀል ሕግ ፤ በገቢ ሕግ ፣ በተጨማሪ እሴት ታክስ ሕግ፣ በጉምሩክ ሕግ የተለያዩ ቅጣት ተደንግጓል፡፡ በአፈፃፀም የሚታዩ ክፍተቶች በመፈተሽ የተቀራረበ የማድረግ ሥራ መሰራት አለበት፡፡

3.2.3 በኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅም ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ለመከላከል የሚያስችል ስልት መዘርጋት አለበት፡፡ የዋስትና ሥርዓት በተለይም የተደራጀ የኮንትሮባንድ ወንጀሎች በተመለከተ ጠበቅ ማለት ይጠይቃል፡፡ በኮንትሮባንድ ጉዳይ በተለይም በተደራጅ አግባብ የሚፈፅሙ ወንጀል ዋስትና ፖኬጅ የሚያደራጅ በመሆናቸው በጥንቃቄ ሊመዘን ይገባል፡፡

3.2.4 በኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ለመመርመር፣ ለመከራከርና ጥራት ያለው ውሣኔ ለመስጠት የሚያስችል አደረጃጀት ፣ ተቋማዊ ብቃትና ሙያዊ ክህሎት፣ እውቀትና አመለካከት ማሳደግ፣

3.2.5 የኢኮኖሚ ነክ ጉዳዮች የሚመለከቱ ችሎቶች ማደራጀት ፤ የተፋጠነ የፍትህ ሥርዓት መዘርጋት

3.2.6 የወንጀሉ ባሕርይ ዓለም አቀፍ ይዘት ያለው በመሆኑ ከሌሎች አገሮችም ቅንጅታዊ አሰራር መፍጠር ያስፈልጋል። እንደአገርም የፍትህ ተቋማትና ነፃነታቸው በጠበቃ መልኩ ተቀራርበው መሥራት አለባቸው።

ዋና ዋና ዋቢ ጽሑፎች

- የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት 1949 የፀደቀ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ
- የኢፌድሪ ሕገመንግሥት 1987 የፀደቀ
- የኢፌድሪ የወንጀል ሕግ 1997 ዓ.ም የፀደቀ
- የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር 541/1999
- የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001
- የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኮ.መ.ቁ 23855፣ 43781፣ የሰጠው ፍርድ
- የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አራዳ ምድብ ችሎት በኮ.መ.ቁ 90851፣ 96023 የሰጠው ፍርድ
- የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ.መ.ቁ 112268 የሰጠው ፍርድ
- የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994
- የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994
- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቀቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 591/2000
- የኢፌዴሪ የተሻሻለው የወንጀል ሕግ ሐተታ ዘምክንያት
- ፀሐይ ወዳ (1994) የወንጀል መሠረታዊ መርሆዎች
- የጉምሩክ ሕግ ዋናዋና ሐሳቦች ለፌደራል ዳኞች የውይይት መድረክ ነሐሴ 2000 ዓ/ም የቀረበ
- ተኸሊት ይመሰል (2004) በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ዋና ዋና ድንጋጌዎች የመወያያ ጽሑፍ፤ ለፌደራል ፍርድ ቤቶች ዳኞች የተዘጋጀ ያልታተመ የመወያያ ጽሑፍ
- Graven, philippe, (1965), an introduction to Ethiopian penal law; Hailesellassie I university.
- Inciardi, ames, (2004) Criminal Justice; 2nd ed university of Delaware
- Serious Economic crime a board room guide to prevention and compliance; white page ltd.
- Kumawat, mahendra; Dimesions of Economic Crimes in India.

- Mehta, Deepa, Economic crime in a globalization society: its impact on the sound development of the state an Indian Perspective
- Bharti, Animesh, Legislative measures to Deal with Economic Crimes In India
- Economic Crime: people, Culture and controls The 4th biennial Global Economic Crime Suryey Transportation and logistics Industry supplement
- Konneh, Amara; (2009) Economic crime, corruption and the conflict in Liberia; policy options for an emerging Democracy and sustainable peace
- Ahmed, Engrmansur, (2001), public private partner ship in the fight against Economic crime; emerging frontiers in corporate social Responsibility.
- Amir, Samavati andetal (2011), Distinctive Features of Economic and Financial crime A study on Iranian.
- Okogbule, Nlerun; The Regulation of Economic Crimes in Nigeria: old problem new challengs and Responses.
- United Nations office on Drugs and Crime: Economic and Financial Crimes: Challengs to sustainable development